***መመሪያ አንድ፡- <u>ከጥያቄ 1 እስከ 10 ድረስ የቀረቡት ጥቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ</u>፡፡***

## ምንባብ

ማሪቱ በለጠ ተወልዳ ካደገችበት ምስራቅ ጎጃም ሞጣ ከተማ ከመጣች ሁለት ዓመት ሊሞላት ጥቂት ቀናት ብቻ እንደቀራት ነገረችኝ፡፡ ከሰውነት ጎዳና የወጣ ፊቷ በድካም የመወየብ ምልክቶች ቢታዩበትም ጠይምና መልከ መልካም ናት፡፡ 13 ዓመት ሆኗታል፡ ያገኘኋት በአዲስ አበባ ሰፊ የቤቶች ግንባታ በሚካሄድበት ቦሌ ክፍለ ከተማ ሲ ኤም ሲ/ሰሚት አካባቢ ነው፡፡ በሞጣ ከተማ እስከ ሁለተኛ ክፍል ተምሬያለሁ ያለችኝ ልበገሯ ማሪቱ፤ ከጎጃም ይዛት የመጣችው አክስቷ ወደ አረብ ሃገር ስትሄድ ለአባቷ ዘመዶች ሰጥታት እንደሄደች አጫወተችኝ፡፡ ነገር ግን አክስቷም ሆነች አሁን የምትኖርባቸው ዘመዶቿ "የተሻለ ትምህርት ቤት እናስገባሻለን" ቢሏትም የትምህርት ቤት ደጃፍን ከረገጠች ድፍን ሁለት ዓመት ሊሆናት ነው፡፡ በዚህም ሁልጊዜ ሆድ ስለሚብሳት ታለቅሳለች፤ ስለ ትምህርትም ስጠይቃት፣በርዕሱ መነሳት ደስተኛ እንዳልሆነች የሚሸሽግ አይኗ ያሳብቃል፡፡

የምትኖርባቸው ዘመዶቿ በዕድሜ ከዕሷ የሚያንሱ ሶስት ልጆች እንዳሏቸው የገለጸችልኝ ማሪቱ እሷግን ቤት ውስጥ ምግብ መስራት፣ ቤት ማጽዳት፣ ልብስ ማጠብ፣ ልጆችን መንከባከብ፣ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ምሳ ዕቃ መቋጠር ወዘተ. የዕለት ተዕለት ሕይወቷ መሆኑን ድካም ባዛለው ድምጿ ነገረችኝ፡፡

ይህ የማሪቱ ታሪክ ከአያት እስከ አየር ጤና፣ ከአዲሱ ገበያ እስከ ቃሊቲ፣ ከልደታ እስከ ቦሌ፣ ከፒያሳ እስከ መገናኛ፣ ከሽሮ ሜዳ እስከ ፈረንሳይ፣ ከጦር ሀይሎች እስከ አስኮ ወዘተ በርካታ የአዲስ አበባ ቤቶችን የሚያንኳኳ፤ የክልል ከተሞችንም የሚነካ እውነታ ነው፡፡ በኢትዮጵያ አሁንም በገጠር ያለው ድህነት ከከተማው የከፋ ነው፡፡ ከኢኮኖሚ ባለፈ ገጠሬው በማህበራዊ አገልግሎቶትም በከተሜው የሚመራ መሆኑ ደግሞ "ከድጡ ወደማጡ" ሆኖ በርካታ የማሪቱ እኩዮች ከተማን እንዲናፍቁ አስገድዷቸዋል፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ማህበራዊ ትስስራችን ጠንካራ በመሆኑ ልጅን ከተማ ያለ ቤተ- ዘመድ ጋር ልኮ ማስተማር የተለመደ ነው፡፡

የወላጅን አደራ ተቀብለው የሚያስተምሩ በርካቶች መኖራቸው የማያጠራጥር ቢሆንም የማሪቱ ዘመዶች አይነት በገጠር አልያም በአነስተኛ ከተሞች ያለ ቤተ-ዘመድን አቅም ማጣት ምክንያት አድርገው የልጆቻቸውን እኩዮች ጉልበት የሚበዘብዙም ቁጥራቸው ቀላል የሚባል አይደለም፡፡

ማሪቱ በጠዋት ተነስታ ወደ ትምህርት ቤት የሚወስዳቸውን አውቶብስ አንድ ሰዓት ላይ ለሚጠብቁት ሶስት ታዳጊዎች ልብስ ማልበስ፣ ቁርስ ማዘጋጀትና የምሳ እቃቸውን መቋጠር

ይጠበቅባታል። በተጨማሪም "ነውር ጌጡ" ለሆኑት የቤቱ ጌቶችም ምግብ ማዘጋጀት፣ ቤት ማፅዳት፣ ልብስ ማጠብ ወዘተ. ደግሞ በተከታታይ የሚጠብቋት ተግባራት ናቸው። ስለዚህ እንደ ጋራ ፊቷ የተቆለለው ስራ ካላለቀ የሚደርስባትን የቁጣ ውርጅብኝ ሽሽት ያለ እረፍት ስትባትል ትውላለች። ገና በለጋነቷ አምስት አባላት ያለውን ቤተሰብ፣ የዕለት ተዕለት ስራ የተሸከመችው ማሪቱ፤ የልጅነት ወዟ እየተመጠጠ መሆኑን እረፍት የራቀውና በስራ ብዛት የደቀቀው ሰውነቷ ይጠቁማል።

ማሪቱ ምንም እንኳን ሰማይ ስለተደፋባት በምትኖረው ኑሮ ደስተኛ ባትሆንም "አድሮ ቃሪያ" የሆነው ሕይወቷ አንድ ቀን ለውጥ ይኖርና ያልፍልኛል በሚል ተስፋ ኑሮዋን መግፋቷ ግን አልቀረም። የማሪቱና መሰሎቿን ሕይወት መቀየር የሚቻለው በሕፃናት እና በሴቶች ላይ ከፍተኛ ጫና ባለባቸው አካባቢዎች፣ የማህበረሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ፤ እንደ ትምህርትና ጤና የመሳሰሉ ማህበራዊ አገልግሎቶችን በማስፋፋት ነው።

1. የትምህርትቤቱን **ደጃፍ** ከረገጠች ድፍን ሁለት ዓመት ሊሆናት ነው።

   ሀ. ሰፈር ለ. በራፍ ሐ. አደባባይ መ. ክፍል

2. ስለትምህርቷ ሲነሳ ደስተኛ እንዳልሆነች የሚሸሽግ አይኗ **ያሳብቃል**።

   ሀ. ይናገራል ለ. ይደብቃል ሐ. ይስቃል መ. ይለምናል

3. እንደጋራ ፊቷ **የተቆለለው** ስራ ካላለቀ የቁጣ መዓት ይወርድባታል።

   ሀ. የተሰበሰበው ለ. የተበተነው ሐ. የተከመረው መ. ሀ ና ሐ መልስ ናቸው

4. የልጅነት ፊቷ **እየተመጠጠ** መሆኑን ሰውነቷ ይጠቁማል።

   ሀ. እያማረበት ለ. እየፈካ ሐ. ወዙ እየጠፋ መ. ወዝ እየተፋ

5. ከሰውነት ጎዳና የወጣው ፊቷ **የመወየብ** ምልክት ቢታይበትም ጠይምና መልከመልካም ናት። ሀ. የመቅላት ለ. የመዋብ ሐ. የመገርጣት መ. የመክሳት

6. የዕለት ከዕለት ሕይወቷ ቤተሰቡን መንከባከብ እንደሆነ **በዛለው** ድምጿ ነገረችኝ። ሀ. በደከመው ለ. በበረታው ሐ. ባማረው መ. በቀጠነው

7. በርካታ የማሪቱ **እኩዮች** ከተማን እንዲናፍቁ አስገድዷቸዋል።

   ሀ. ባልደረቦች ለ. ቤተሰቦች ሐ. ዘመዶች መ. መሰሎች

8. ልጅን ከተማ ያለ ዘመድ ጋር **ልኮ** ማስተማር የተለመደ ነው።

   ሀ. አስገብቶ ለ. ሰዶ ሐ. አስተላልፎ መ. አምጥቶ

9. የሚደርስባትን የቁጣ ውርጅብኝ ሽሽት ያለ እረፍት **ስትባትል** ትውላለች።

   ሀ. ስትለፋ ለ. ስትሰራ ሐ. ስትደክም መ. ሁሉም

10. ማሪቱ ገና **በለጋነቷ** አምስት አባላት ያለውን ቤተሰብ ስራ ተሸከመች።

    ሀ. በህፃንነቷ ለ. በወጣትነቷ ሐ. በጮርቃነቷ መ. በቀንበጥነቷ

***መመሪያ ሁለት፡- <u>ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ምረጡ</u>፡፡***

11. ሥነ-ግጥም ማንኛውንም **<u>አልባሌ</u>** ቃል ዝም ብሎ አያጉርም ሲል የተሰመረበት ቃል ትርጉም ሀ. ከባድ ለ. ቀላል ሐ. ተራ መ. ዋጋ ቢስ
12. በልምድና በግንዛቤ **<u>ጉድለት</u>** ምክንያት በብዙ ቤተሰቦች ለቤተሰብ የጋራ ማዕድ ትኩረት አይሰጡም።
    ሀ. እንክን ለ. ብልሽት ሐ. አለማሟላት መ. እጥረት
13. በቆሎው **<u>እንጭጭ</u>** ስለሆነ ሲበሉት ይጣፍጣል፡፡
    ሀ. እሸት ለ. ብዙ ሐ. ለጋ መ. አጭር
14. የየራሳቸውን ሐሳብ በሚያራምዱ አንቀጾች የተገነባ የድርሰት ዋና ሐሳብ የሚተላለፍበት የድርሰት ክፍል የትኛው ነው?
    ሀ. ሐተታ ለ. ርዕስ ሐ. መደምደሚ መ. መግቢያ
15. "ለንግግር አድማጭ እንዳለው ሁሉ ለድርሰትም ____________________አለው?" በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ ሐሳቡን በትክክል ሊያሟላ የሚችለው ከሚከተሉት አማራጭ የትኛው ነው?
    ሀ. ርዕስ ለ. ፀሐፊ ሐ. አናጋሪ መ. አንባቢ
16. "ከነባሩ ትውልድና ከአሁኑ ትውልድ ጠንካራ የሃገር ፍቅር ስሜት ያለው የትኛው ነው?" በሚል የሚቀርብ ሐሳብ የሚፃፍበት የድርሰት አይነት ከሚከተሉት የትኛው ነው?
    ሀ. ተራኪ ለ. አመዛዛኝ/አከራካሪ ሐ. ገላጭ መ. ስዕላዊ
17. አንድ ሰው "ማር አልስም" ብሎ ተናገር ፣ ምንን እንደሚያመለክት በተሰጡት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?
    ሀ. መጥገብን ለ. መደሰትን ሐ. መወጠርን መ. መዝናናትን
18. በቃል የሚቀርብ ፈተና ውጤታማ ለመሆን በጣም ጠቃሚ ይሆነው ክሂል ከሚከተሉት አማራጮ መካከል የትኛው ነው?
    ሀ. የመናገር ለ. የመጻፍ ሐ. ማንበብ መ. ማዳመጥ
19. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በመጥበቅና በመላላት የተለያዩ ትርጉሞች ሊያስገኝ የሚችለው ቃል የትኛው ነው?
    ሀ. መሶብ ለ. መቀስ ሐ. መርፌ መ. መጋዝ
20. ተማሪዎች በፈተና ወቅት በአብዛኛው የሚጠቀሙበትን የንባብ አይነት ከሚከተሉት አማራጭ መካከል የትኛው ነው?
    ሀ. የዝግታ ለ. የፍጥነት ሐ. የአሰሳ መ. የገረፍታ

21. "አንድ **<u>ቀንደኛ</u>** ካለ ሁሉም ሲታመስ ይውላል" በሚለው ዓ.ነገር ውስጥ የተሰመረበት ፈሊጣዊ አነጋገር ትርጉም ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

ሀ. አዋኪ ለ. አስረኛ ሐ. አደገኛ መ. አዋጊ

22. **አገሬ ቆላ ነው ፣ ደጋ ወይና ደጋ**

**እዚያ ብርሃን አለ፣ ሌሊቱ ሲነጋ**

**አገሬ ተረር ፣ ሸለቆ ረባዳ**

**አገሬ ጅረት ነው ፣ ገደልና ሜዳ**

በሚለው በግጥም ውስጥ ያሉት ስንኞች ባለ ስንት ሐረጎች ናቸው፡፡

ሀ. አንድ ለ. ሁለት ሐ. ሶስት መ. አራት

23. ተማሪ መሃመድ ወድቆ ያገኘውን ውድ ዕቃ በታማኝነት ለርዕስ መምህሩ አስረከበ፡፡ ርዕስ መምህሩ ጉዳዩን በሚመለከት ለመሃመድና ለቤተሰቦቹ ደብዳቤ ቢፅፉ፤ የሚፅፉት ደብዳቤ ከየትኛው ይመደባል?

ሀ. የሽልማት ለ. የምስጋና ደብዳቤ ሐ. የማመልከቻ ደብዳቤ መ. የቅሬታ ደብዳቤ

24. **<u>አያት</u>** ና ወደዳት ፤ የሴትም ሆነ የወንድ አያት የለውም፡፡ የተሰመረበትን በሚመለከት ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የመጀመሪያ መመልከት የሚል ፍቺ አለው፡፡

ለ. የመጀመሪያው ጠብቆ ሲነበብ ሁለተኛው ላልቶ ይነበባል፡፡

ሐ. ሁለተኛው የእናት እናት ወይም የአባት አባት የሚል ፍቺ አለው፡፡ መ. የመጀመሪያው ላልቶ ሲነበብ ሁለተኛው ጠብቀ ይነበባል፡፡

25. ከሚከተሉት መካከል የንግግር አቀራረብ መመሪያ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ርዕስን ማስተዋወቅ ሐ. ሁሉንም ነገር አለማንበብ

ለ. ምስጋና ማቅረብ መ. ልምምድ ማድረግ

26. "ልጄን ቁራኛ የተቆራኘው መሆኑን ነው አገር አውግቶ የጨረሰ?" አለ **<u>በተሰበረ</u>** ድምጽ፡፡ በሚለው ዓ.ነገር ውስጥ ለተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ፍቺ የያዘው የትኛው ነው?

ሀ. በተከፈለ ለ. ባዘነ ሐ. በተለሳለሰ መ. በተበሳጨ

27. "አባባል" ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቺ የሚሆነው?

ሀ. ብሂል ለ. አስተሳሰብ ሐ. ምልልስ መ. ሃሜት

28. ከሚከተሉት ዓ.ነገሮች መካከል ስለ ቃላዊ ግጥም ትክክለኛ ሃሳብ የያዘው የትኛው ነው? ሀ. ደራሲው በስም ይታወቃል ሐ. ይነገራል/ይዜማል

ለ. የማህበረሰቡን ሃሳብ የሚገልፅ አይደለም መ. ከጽሁፋዊ የተለየ የቤት አመታት አለው

29. ከሚከተሉት አንዱ ስለተጻፈ ግጥም ትክክለኛ ሃሳብ ያልያዘው ቃል አማራጭ የትኛው ነው? ሀ. ቃላቱ ማራኪና ቁጥብ ናቸው

ለ. በጥቂት ቃላት ብዙ መልእክት ያስተላልፋል ሐ. ግጥም በስንኝ ይመጠናል

መ. ደራሲው አይታወቅም

30. ከሚከተሉት ዓ.ነገሮች አንዱ ስለ አከራካሪ ድርሰት ትክክለኛ ሃሳብ የያዘ ነው። ሀ. የአንድን ነገር ጠንካራና ደካማ ጎን እያነጻጸረ ያቀርባል

ለ. አንድ ነገር ከምን ከምን እንደተሰራ ለማስረዳት እንጠቀምበታለን ሐ. አንድ ድርጊት በጊዜና በድርጊት ቅደም ተከተል ያቀርባል

መ. አንድን ድርጊት በአይነ ህሊና እንዲታይ አድርጎ የሚያቀርብ ነው

31. ከሚከተሉት አንዱ የንግግር አቀራረብ መመሪያ ውስጥ ይመደባል።

ሀ. ርዕስን መረዳት
ሐ. በተሰጠን የጊዜ ገደብ ንግግሩን መቋጨት

ለ. መረጃ መሰብሰብ
መ. ቢጋር መንደፍ

32. በሐረግ 6 በስንኛ 12 የቀለማትን የያዘው የግጥም አይነት የትኛው ነው? ሀ. የቡሄ በሉ ቤት ግጥም
ሐ. የወል ቤት ግጥም

ለ. የሰንጎ መገን ቤት ግጥም
መ. የጸጋዬ ቤት ግጥም

33. _______________ ፊት ለፊት በግልጽ ተለይቶ የሚታይ ትርጉም ነው።

ሀ. ህብረቃል ለ. ወርቅ ሐ. ቅኔ መ. ስም

34. ወረግቡ ለሚለው ፈሊጣዊ አነጋገር ተመሳሳይ የሚሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ድርስ ለ. እርጉዝ ሐ. ቀፈታም መ. ወፍራም

35. ሥነ ቃል ከአንዱ ወደ አንዱ በመንገር ይተላለፋል። በዚህን ጊዜ እንደ ሁኔታው የመቀያየር እድሉ ሰፊ ነው። ይህ በየትኛው ጠባዩ ይገለጣል።

ሀ. ተደጋጋሚነት ለ. አፋዊነት ሐ. የወል ሀብትነት መ. ተለዋዋጨነት

36. "ይገርማል" የሸቀጥ ዋጋ እንዲህ ይናር!" አባባሉ ምን ይገልጻል?

ሀ. አድናቆትን ለ. ትዝታን ሐ. እልህን መ. መሬትን

37. ዳኛው ተከሳሹን ለሚቀጥለው ቀጠሮ <u>**ጠበቃውን**</u> ይዞ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጡ።

ሀ. ዋሱን ለ. ነገረ ፈጅን ሐ. ምስክሩን መ. ግለሰቡን

38. የሥነ- ቃል ባለቤቱ___________________ ነው

ሀ. ደራሲው ለ. ድምጻዊው ሐ. ሕዝቡ መ. ግለሰቡ

39. የሁላችንም **<u>ቀልብ የማረከ</u>** ነገር ተከሰተ። ለተሰመረበት ሐረግ ተመሳሳይ ሊሆን የሚችለው ቃል የትኛው ነው?

ሀ. የነተተ ለ. የሳበ ሐ. ያስለቸ መ. ያተኮረ

40. ልጁ ዘወትር የባጥ የቆጡን **<u>ይዘላብዳል</u>**። ለተሰመረበት ቃል በይበልጥ ተመሳሳይ የሆነው ፍቺ የቱ ነው?

ሀ. መናገር ለ. መቀባጠር ሐ.መለፍለፍ መ. ለ እና ሐ

41. ሚካኤል **<u>ከመቅጽበት</u>** ከአካባቢው ተሰወረ። ለተሰመረበት ሐረግ ተቃራኒ ፍቹ ከሚከተሉት የትኛው ነው?

ሀ. ወዲያውኑ ለ. ከአፍታ ሐ. በእርጋታ መ. በፍጥነት

42. ኢትዮጵያ ውስጥ **<u>ትኩስ ሃይል</u>** በብዛት ይገኛል። ለተሰመረበት ሐረግ ተመሳሳይ የሆነው ፍቺ የቱ ነው?

ሀ. ወጣት ለ. ወንበዴ ሐ. አዛውንት መ. ባልቴት

43. ትውልድ ከሥነ-ምግባር እንዳያፈነግጥ **<u>መግቻ</u>** ያስፈልገዋል። ለተሰመረበት ቃል ተቃራኒ የሆነው ፍቺ የቱ ነው?

ሀ. መቆጣጠሪያ ለ. መያዣ ሐ. መቆሚያ መ. መልቀቂያ

44. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ከሌሎች ጋር በፍቺ የማይመሳሰለው ቃል የትኛው ነው? ሀ. አበጠ ለ. ተነፈገ ሐ. ተቀበተተ መ. ተነፋ

45. ከሚከተሉት አንዱ በድርሰት አጻጻፍ መመሪያ ውስጥ ይካተታል።

ሀ. ያልተሟሉ ዓ.ነገሮች መጠቀም ሐ. ሃሳብን በቅደም ተከተል ማደራጀት ለ. ሥርዓት ነጥብን በአግባቢ አለመጠቀም መ. ቃላትን በዘፈቀደ መጠቀም

46. "ማንበብ ፣ ማሰብ ፣ መጠየቅ በቀላሉ አሉታዊ አስተሳሰብ እንዳያጠቃን ያደርጋል።" በሚለው ዓ.ነገር ውስጥ በምክንያትን የተጠቀሰው የቱ ነው?

ሀ. ማንበብ ፣ ማሰብና መጠየቅ ሐ. አሉታዊ ሃሳብ ላለመጋለጥ ለ. አሉታዊ አስተሳሰብ መ. አውንታዊ ሐሳብ ማዳበር

47. "ሁሉም ተፈውሷል" የሚለው ሐረግ ፍቹ ______________________ ነው።

ሀ. ሁሉም ድኗል ሐ. ሁሉም አልቅሷል

ለ. ሁሉም ተይዟል መ. ሁሉም አቅም አጥቷል

48. ከሚከተሉት ዓ.ነገሮች መካከል ሰዋሰው ትክክል ያልሆነው ዓ.ነገር የቱ ነው? ሀ. ሀኪሞች በሽተኞች ያክማሉ። ሐ. በግ ሳር ይግጣሉ።

ለ. የነገውን ስልጠና በነቃ መንፈስ እከታተላለሁ። መ. አቶ በዓሉ ግርማ ደራሲ ናቸው

49. ከሚከተሉት ዓ.ነገሮች መካከል አንዱ የቦታ አመልካች ተውሳከ ግስን የሚሳይ ነው? ሀ. ሁሉም ተማሪዎች ለፈተና ተዘጋጅተዋል፡፡
 ለ. ተማሪዎች በሁሉም ትምህርት ዘርፍ የቀረበላቸውን ፈተና ነገ ይጨርሳሉ፡፡ ሐ. ተማሪዎቹ እዚህ ነበሩ፡፡
 መ. የፈተና ውጤት በየትምህርት ቤቱ እንደሚለጠፍ ተገለጸ፡፡
50. ቀጥሎ በቀረበው ቅኔ ውስጥ ህብረቃሉ የቱ ነው? ይማርልኝ
 ብዬ ዋሽራ ሰድጄ፣
 ቀለም ገባው አሉ እሳት ሆነ ልጄ፡፡
 ሀ. ዋሽራ ሰድጄ ለ. ይማርልኝ ሐ. ቀለም ገባው መ. እሳት ሆነ ልጄ
51.ቀጥሎ በቀረበው ቅኔ ውስጥ ወርቁ የቱ ነው? ተደስቼ
 ነበር ባለፈው ክረምት፣
 ዛሬስ ሆዬን ከፋው ደመና ሲቀር፡፡
 ሀ. ዘነበ ለ. በሰማይ ላይ ደመና ታየ ሐ. ሳይዘንብ ቀር መ. ደም መና
52. ቀጥሎ በቀረበው ቅኔ ውስጥ ሰሙ የቱ ነው? ሀገሬ
 አታልሽ እኔ አሳይሻለሁ
 ከጂማ መኖሩን በአይኔ አይቻሁ፡፡
 ሀ. ጅማ ሃገር ለ. ሃገር ሐ. ከዳተኛ መ. ከጂ
53. ከሚከተሉት የድርሰት ክፍሎች ወደ ዋናው ጽሁፍ መተላለፊያ በር ነው፡፡
 ሀ. መግቢያ ለ. ሐተታ ሐ. መደምደሚያ መ. ርዕስ
54. ከሚከተሉት ውስጥ የማዳመጥ እንቅፋት የሆነው የቱ ነው?
 ሀ. ያለ ጆሮ ማዳመጥ ሐ. ዝምታን ማዳመጥ
 ለ. ስሜታዊነት መ. ይሁነኝ ብሎ መስማት
55. በአንድ ቅኔ ዉስጥ ወርቅ የምንለዉ
 ሀ. በሰም የተሸፈነዉን ነዉ ሐ. ፈርጥ ስለሆነ ነዉ
 ለ. ምስጢሩን ነዉ መ. ሀ እና ለ

***መመሪያ ሦስት፡- <u>ከጥያቄ 56-60 እስከ ድረስ ያሉትን ጥያቄዎች በግጥሙ መሰረት</u>፡፡***

“ዘር ከልጓም” ስለሳበኝ፣ ባፈር
ምድር ዛሬን ሳገኝ፣ አራት
ሚሊዮን አነሰኝና፣

እንድትኖርልኝ እንደገና፣
"እድሜ ለአጥነት" አልኩ ሳላውቀው፣ ልቤን ደስታ
አሞቀው።

*(ስለሞን ወሌ፣ ቃና ጥበብ)*

56. ግጥሙ የተዋቀረው በስንት ስንኞች ነው?

ሀ. በሶስት ለ. በስድስት ሐ. በዘጠኝ መ. በአራት

57. ግጥሙ የተጻፈበት ዓላማ____________________ ነው?

ሀ. ለማሞገስ ለ. ለመቃወም ሐ. ለመጠየቅ መ. ለማግባባት

58. ግጥሙ ውስጥ በስንት መነሻ ሐረጎች አሉት?

ሀ. ስድስት ለ. አስራ ሁለት ሐ. ስምንት መ. ሃያ አራት

59. በግጥሙ ውስጥ ባሳድስ ፊደሎች የሚጨርሱ ስንኞች ስንት ናቸው?

ሀ. ስድስተ ለ. ሶስት ሐ. ሁለት መ. አራት

60. የሁለተኛው ስንኝ መነሻ ሐረግ ከሚከተሉት የትኛው ነው?

ሀ. ባፈር ምድር ለ. ዛሬን ሳገኝ ሐ. እድሜ ለአጥነት መ. ዘር ከልጓሙ

***መመሪያ አራት፦ <u>ከጥያቄ ቁጥር 61-69 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሠረቱ ናቸው:: ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ</u>::***

*ኢትዮጵያ በምስራቅ አፍሪካ የምትነኝ ሀገር ስትሆን በርካታ ህዝብ ካላቸው የዓላም ሀገሮች ተርታ ትሰለፋለች። ሀገሪቱ በደቡብ ከኬኒያ ጋር በምስራቅ ከጅቡቲ ጋር በሰሜን ከኤርትራ ጋር በምዕራብ በኩል ከደቡብና ሰሜን ሱዳን ሀገሮች ጋር በድንበር ትዋሰናለች። ኢትዮጵያ እንደ አባይ ፣ ዋቢ ሸበሌ ፣ አዋሽ ፣*
*ደዴሳና በለስን የመሣሠሉ ታላላቅ ወንዞች ባለቤት ከመሆኗ በተጨማሪ እነ ጣናን እና ባቦጋያን የመሳሰሉ ታላላቅ ሀይቆችም ባለቤት ናት።*

*ኢትዮጲያ የአክሱም ሀውልት ፣ ጎንደር ጉዛራና ፋሲለደስ ፣ ላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስትያን ፣ ጭስ አባይ ፏፏቴ ፣ የሰሜን ብሔራዊ ፓርክ ፣ የሶፍ ኡመር ዋሻ ፣ የኮንሶ ህዝብ ጥንታዊ የእርከን ስራ ፣ የሀርላ ህዝብ ጥንታዊ ሳንቲሞችና ቁሳቁሶች ፣ እንዲሁም በቅርቡ የተመዘገበውን የመስቀል በዓል አከባበር የገዳ ሥርዓትን ጨምሮ ሌሎች በርካታ ቅርሶችን በዓለም የቅርስነት መዝገብ ውስጥ በማስፈር ከአፍሪካ ቀዳሚ የሆነች ሀገር ነች።*

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ ኢትዮጵያ የራሷ የሆነ የጽሑፍ ፊደል ፣ ቁጥርና የዘመን አቆጣጠር ያሏት እንዲሁም ከዓለም ሀገሮች ሁሉ በማንም ወራሪ ቅኝ ያልተገዛች ብቸኛ የጥቁርሮች መኩሪያና መመኪያ የሆነች ነፃ ህዝብና መንግስት ያላት ሀገር ነች።

61. ከላይ ለቀረበው ድርሰት ተስማሚ የሚሆነው ርዕስ ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ነው? ሀ. የኢትዮጲያ ወንዞች

ሐ. ኢትዮጲያ

ለ.የኢትዮጲያ ቅርሶች መ. የኢትዮጲያ ሀይቆች

62. ምንባቡ የተፃፈበት የድርሰት ማፃፊያ መንገድ የያዘው አማራጭ የቱ ነው? ሀ. አስረጂ ድርሰት

ሐ.ስዕላዊ ድርሰት

ለ.አመዛዛኝ ድርሰት መ.ተራኪ ድርሰት

63. ከሚከተሉት አንዱ የኢትዮጲያ ወንዞች ተብለው ከተዘረዘሩት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው? ሀ. ጣና ለ. አባይ

ሐ. ዋቢ ሸበሌ መ. በለስ

64. ኢትዮጲያን በስተምስራቅ እና በስተምዕራብ የሚያዋስኗት ሀግሮች በቅደም ተከተላቸው መሠረት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ሱዳን ፣ ጅቡቲ ለ.ጅቡቲ ፣ ሱዳን ሐ. ኬኒያ ፣ ጅቡቲ መ. ጅቡቲ ፣ ኤርትራ

65. ኢትዮጲያ በስተሰሜን እና በስተደቡብ የሚያዋስኗት ሀገሮች በቅደም ተከተላቸው መሠረት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ኤርትራ ፣ ኬኒያ ለ. ኬኒያ ፣ ኤርትራ ሐ. ሱዳን ፣ ኤርትራ መ. ኤርትራ ፣ ሱዳን

66. ከሚከተሉት ውስጥ ኢትዮጲያን በቅርብ ግዜ በቅርስነት ካስመዘገበችው ቅርሶች ውስጥ ይጠቀሳል? ሀ. የአክሱም ሀውልት

ሐ.ፋሲለደስ

ለ. የመስቀል በአልና የገዳ ሥርዓት መ.የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያን

67. ኢትዮጵያ የጥቁሮች መመኪያ እና መኩሪያ ነፃ ሀገር እንድትሆን ያስቻላት ምክንያት ምንድን ነው?

ሀ. ታሪካዊ ቅርሶቿ አስደናቂ መስህቦቿ ለ. የራሷ

የሆነ የፅህፈት ፊደል ስላላት ሐ. በማንም ወራሪ ቀኝ

ያልተገዛች መሆኗ መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው።

68. ድርሰቱ በስንት አንቀፅ የተዋቀረ አንቀፅ ነው?

ሀ. በአራት ለ. በሦስት ሐ. በአምስት መ. በሁለት

69. ከሚከተሉት ውስጥ የአንቀፅ ሁለትን ዋና ሀሣብ የያዘው አማራጭ የቱ ነው? ሀ. ኢትዮጲያ የራሷ የሆነ የአፃፃፍ ስርአት አላት
ለ. ኢትዮጲያ በርካታ ቅርሶችን በዓለም የቅርስነት መዝገብ አስፍራለች ሐ. ኢትዮጲያ በርካታ ህዝብ ያላት ሀገር ናት
መ. ኢትዮጵያ ሉአላዊት ሀገር ናት

**መመሪያ አምስት፦ ከጥያቄ ቁጥር 70-115 ድረስ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ አራት አራት አማራጮች ቀርበዋል፤ ከነዚህ አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።**

70. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ አንቀፅ ትክክል የሆነው የቱ ነው?
ሀ. ከብዙ ዓ.ነገሮች እና ጥቂት ሀይለቃሎችን በመያዝ ይገነባል። ለ. ከጥቂት ዓ.ነገሮች እና ከብዙ ሀይለ ቃሎች ይገነባል።
ሐ. ከብዙ ዓ.ነገሮች እና ከብዙ ከብዙ ዓ.ነገሮች ይገነባል። መ. ከጥቂት ዓ.ነገሮች እና ከአንድ ሀይለ ቃል ብቻ ይገነባል።

71. በቋንቋ ውስጥ ዝቅተኛው ባለትርጉም አዘል ቅንጣት ____________________ ይባላል፡፡
ሀ. ፊደል ለ. ሆሄ ሐ. ምዕላድ መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው፡፡

72. ከሚከተሉት ውስጥ ውስጠ ግንድ ቅጥያን የያዘው ቃል የቱ ነው?
ሀ. ከሄደ ለ. ከመጣች ሐ. ከሰባበረ መ. ሴቶች

73. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ተውኔት ትክክል ያልሆነው የቱ ነው? ሀ. ተውኔት አንዱ የሥነ ፅሁፍ ዘርፍ ነው፡፡
ለ. ተውኔት የደራሲው የምናብ አለም ፈጣራ ሆኖ በገቢር ይቀርባል። ሐ. ተውኔት በትዕይንት ተከፋፍሎ ይቀርባል፡፡
መ. በተውኔታዊ ድርሰት እና በልቦለድ ፅሁፍ መካከል ምንም ልዩነት የለም።

74. አንድ ድርጊት እና ባህሪ ከሌላ ድርጊት እና ባህሪ ጋር ተለይቶ የታወቀ መሆኑ ወይም አለመሆኑን ለይቶ የሚጠቁም (የሚያሳይ) የቃል ክፍል ምን ይባላል?
ሀ. ገላጭ ለ. መስተዐምር ሐ. መስተፃምር መ. ግስ

75. ከሚከተሉት ውስጥ በአሉታዊ ዐ/ነገር ቅርፅ የቀረበው አረፍተ ነገር የቱ ነው? ሀ. ሀና ምሳ አልበላችም፡፡
ሐ. ሀና ምሳ የት በላች?
ለ. ሀና ምሳ መብላት ፈለገች፡፡ መ. ሀና ምሳ በላች፡፡

76. ከሚከተሉት ዐ/ነገሮች ውስጥ ስለ አንቀፅ ትክክል ያልሆነው ሀሳብ የቱ ነው? ሀ. አንቀፅ የሀሳብ አንድነት
እና ግጥምጥምነት ያላቸውን ዐ/ነገሮች ይይዛል። ለ. አንቀፅ በአንድ ግዜ ሁለትና ከዚያ በላይ ኃይለ ቃል
ይይዛል።
ሐ. አንቀፅ ሲፃፍ ህዳጉ ገባ ተብሎ ይጀመራል። መ.ሁሉም
ዐ/ነገሮች ትክክል ናቸው።

77. ከሚከተሉት ውስጥ የውይይት አቀራረብ መመሪያ ያልሆነው የቱ ነው? ሀ. ርዕሱን
በመገንዘብ መረጃ መሰብሰብ
ለ. የውይይቱን ርዕስ ማስተዋወቅ
ሐ. ከተፈቀደልን የግዜ ገደብ በላይ መጠቀም
መ. ሀሳባችን ተቀባይነት እንዲያገኝ በቂ ምክንያት ማቅረብ

78. "ያ የኔ መፀሀፍ ነው።"በሚለው ዐ/ነገር ውስጥ በመሙያነት የገባው ስም የቱ ነው?
ሀ. እኔ ለ. ያ ሐ. መፀሀፍ መ. ነው

79. ከሚከተሉት ውስጥ በክርክር ግዜ ትኩረት ከሚሰጥባቸው ነጥቦች መካከል ይመደባል። ሀ. የሌላውን ተከራካሪ
ሀሳብ አለማንቋሸሽ
ለ. ለተከራካሪ ሀሳብ በምክንያት መልስ መስጠት ሐ. ተራን
ጠብቆ መናገር
መ. ሁሉም መልሶች ናቸው።

80. ቃልን ከቃል፣ሀረግን ከሀረግ እና ዐ/ነገርን ከዐ/ነገር የሚያጣምር የቃል ክፍል____________________ይባላል? ሀ. ሀረግ
ለ. መስተአምር ሐ. መስተፃምር መ. ግስ

81. "አመነታን "የሚለው ግስ በስንተኛ መደብ፣ቁጥርና ፆታ እንደተገለፀ ትክክለኛ መልስ የያዘው አማራጭ የቱ ነው?
ሀ. አንደኛ መደብ፣ብዙ ቁጥር፣ፃታ አይለይም ለ. ሶስተኛ
መደብ፣ብዙ ቁጥር፣ፃታ አይለይም ሐ. ሁለተኛ መደብ፣ብዙ
ቁጥር፣ፆታ አይለይም መ. አንደኛ መደብ፣ነጠላ ቁጥር፣አንስታይ
ፆታ

82. ከሚከተለው ውስጥ ስለ ሥርዓተ ነጥቦች አገልግሎት ትክክል የሆነው የቱ ነው? ሀ. ሥርዓተ ፅህፈትን
በአግባቡ ለመከወን
ለ. አንድ ፅሁፍ የያዘውን መልክት በትክክል ማስተላለፍ እንዲችል ሐ .በፅሁፍ ውስጥ
የጎላ አገልግሎት የላቸውም
መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው።

83. ከሚከተሉት ሥርዓተ ነጥቦች ውስጥ ጥምር ቃልን ለመመስረት የሚያገለግለው ሥርዓተ ነጥብ የቱ ነው?

    ሀ. << >> ለ. ( ) ሐ. _ መ. /

84. በፅሁፋችን ውስጥ ጅምር ወይም ያላለቀ ሀሳብ መኖሩን እና አንባቢው በራሱ ሀሳብ እንዲሞላ ስንፈልግ የምንጠቀመው ሥርዓተ ነጥብ የትኛው ነው?

    ሀ. << >> ለ. ... ሐ.፣ መ.፤

85. ስለ አንድ ነገር አሰራር ወይም ምንነት እና ዝርዝር ሁኔታ የሚገለፅበት የድርሰት አይነት የቱ ነው?

    ሀ. አስረጂ ድርሰት ለ. አመዛዛኝ ድርሰት ሐ. ስዕላዊ ድርሰት መ. ተራኪ ድርሰት

86. "የተባበሩት መንግስታት ድርጅት" በአፅፅሮተ ቃል አጥሮ ሲፃፍ ትክክለኛ መልስ የያዘው አማራጭ የቱ ነው?

    ሀ. የ.ተ.መ.ድ ለ. ተ.መ.ድ ሐ. የተ.መ.ድ መ. የተ.መን.ድ

87. "ይመጣል"የሚለው ቃል ውስጥ የገባው ግዜ አመልካች ቅጥያ የሚያመለክተው ግዜ የትኛውን ግዜ ነው?

    ሀ. ኀላፊ ግዜን ሐ. ኢ-ኀላፊ ግዜን
    ለ. የትንቢት ግዜ መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው።

88. ከሚከተሉት ውስጥ የተውኔት አላባ ያልሆነው የቱ ነው?

    ሀ. ገፀ-ባህሪ ለ. መቼት ሐ. ትዕይንት መ. ሴራ

89. "አበጀህ ለመሆኑ እንዴት ሰራህው በዚህ ዕድሜህ ግዜህን ጉልበትና ገንዘብህን ሳትቆጥብ የስፌት መሣሪያ መፍጠርህ አስደስቶኛል" ከላይ ያለ ሥርዓተ ነጥብ በተፃፉት ዐ/ነገሮች ውስጥ የተገደሉትን ሥርዓተ ነጥቦች በቅደም ተከተላቸው የያዘው አማራጭ ከሚከተሉት ውስጥ የትኛው ነው?

    ሀ. !,?,፣,። ለ.፣,?,!,። ሐ.?,፣,!,። መ.!,፣,?,።

90. "-ኦች" የሚለው አብገር ቅጥያ የተቀጠለበት ስም ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው? ሀ. በሬዎች ለ. ሰዎች ሐ. ጠረጴዛዎች መ. በቅሎዎች

91. ከሚከተሉት ቃላት መካከል በትርጉም ልዩ የሆነው የትኛው ነው?

    ሀ. ጥንድ ለ. ሌጣ ሐ. ብቸኛ መ.ነጠላ

92. "አይኑ ተንከራተተ" ብለን ጓጓ ካልን "አይኑ ተጎለጎለ" ብለን ምን አንላለን?

    ሀ. ተንበለጠጠ ለ. ቀላወጠ ሐ. ደነገጠ መ. ተገላበጠ

93. "እክስቴ ጠንክራ ብትሰራም ጎበዝ ነጋዴ አይደለችም።"በሚለው ዐ/ነገር ውስጥ በስም መሙያነት የገባው ሀረግ የቱ ነው?

ሀ. ጠንካራ ብትሆንም ለ. ጎበዝ ነጋዴ ሐ. ብትሆንም መ. አይደለችም

94. "መናገር ቻለ ወይም ጀመረ "ለሚለው አገላለፅ አቻ ትርጉም ያለው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

ሀ. አፉን ፈታ ለ. አፉን አናገረ ሐ. አፉን አሻረ መ. አፉን አሳየ

95. የተውኔት ፅሁፍ (ድርሰት) በመፃፍ (በመድረስ) የሚታወቅ ሰው ምን ይባላል?

ሀ. ገፀ-ባህሪ ሐ. የመድረክ ገፅ ባለሙያ

ለ. አዘጋጅ መ. ፀሀፊ ተውኔት

96. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ተውሳከ ግስ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ይሁን እንጂ ለ. ክፉኛ ሐ. ቶሎ ቶሎ መ. ትላንት

97. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ መጠይቃዊ ቃላትን የያዘው አማራጭ የቱ ነው?

ሀ. ማን፣ምን፣ለምን፣እንዴት ሐ. የት፣እንዴ፣መቼ ፣ማ

ለ. እሱ፣እሷ፣እኔ መ. A እና C መልስ ናቸው

98. በግጥም ውስጥ ስለ አንድ ሀሳብ የሚገልፅ የስንኞች ስብስብ ምን ይባላል?

ሀ. አንጓ ለ. ሐረግ ሐ. ስንኝ መ. ምት

99. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ግጥም ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ግጥም የብርቱ ስሜት መግለጫ ነው

ለ. ግጥም ከዝርው በበለጠ የቃላት ምርጫን ይጠይቃል

ሐ. ግጥም ቤት መምቻ እና ቤት መድፊያ ቃላት አሉት መ. ግጥም

ዜማዊ አይደለም

100. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ቃሉ ሳይጠብ እና ሳይላላ ቃሉን በማንብ እና በአገባብ ሁለት ፍቺ የሚሰጠን ቃል የቱ ነው?

ሀ. በራ ለ. ለፋ ሐ. ገና መ. ሰባ

101. "ወንፊት" የሚለው ቃል ፍካሬያዊ ፍቺ ሊሆን የሚችለው ከሚከተሉት ውስጥ የቱ ነው?

ሀ. የፅህል ማጣሪያ ሐ. ምርት ከግርድፍ መለያ

ለ. ወሬ ማይቋጥር መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው።

102. ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን በማንሳት አንዱ ካንዱ የሚበልጥበትን፣የሚሻልበትን እና የሚለይበትን ነገር በማንሳት በማወዳደር እና በማነፃፀር የሚፃፍ የድርሰት አይነት_______________ይባላል። ሀ. ተራኪ ድርሰት ለ. ስዕላዊ ድርሰት ሐ. አመዛዛኝ ድርሰት መ. አስረጂ ድርሰት

103. ከሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች መካከል በመልክቱ የተለየው የትኛው ነው?

ሀ. ሴት ሚቷ በማጀቷ

ሐ. ሴት ለቤት ወፍጮ ለዱቄት ለ.

ከሚስት ጋር ያበረ ከእግዜር የተማከረ

መ. ሴት በዛ ጎመን ጠነዛ

104. ከሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች መካከል ልጆችን የሚያሞግስ ምሳሌያዊ አነጋገር የቱ ነው?

ሀ. ልጅና ወረቀት የያዘውን አይለቅም

ሐ. ልጅ ይሮጣል እንጂ አባቱን አይቀድምም ለ. ልጅና

ጦጣ ውሃ ይጠጣ

መ. ልጅ ካበጀው አባት ያበላሸው

105. "ልጅ ያለ እናት፣________________" ክፍት ቦታውን የሚተካው የተጎደለውን ምሳሌያዊ አነጋገር የሚያሟላው አማራጭ የቱ ነው?

ሀ. አይፈጠርም ለ. ቤት ያለ ጉልላት ሐ. ያፈራል ጠላት መ. ያመጣል ጠላት

106. "የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል"ለሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር በይዘት (በመልክት) ተመሣሣይ የሆነው ምሳሌያዊ አነጋገር የትኛው ነው?

ሀ. ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል

ሐ. ሞኝ በብልህ ይስቃል

ለ. ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል

መ. ወንድ ወደ ችሎት ሴት ወደ ማጀት

107. የፈሪ እናት ታስታውቃለች፣

አፋፍ ላይ ሆና ተው ሽሽ ትላለች፣ የጎበዝ እናት

ታስታውቃለች፣ እመሀል ገብታ በለው ትላለች።

ከሚከተሉት ውስጥ ከላይ የቀረበው ቃላዊ ግጥም የሚካተተው ከየትኛው የቃላዊ ግጥም አይነት ውስጥ ነው?

ሀ. የሙሾ ቃላዊ ግጥም

ሐ. የሰርግ ቃላዊ ግጥም

ለ. የፉከራ ቃላዊ ግጥም

መ. የልመና ቃላዊ ግጥም

108. ከሚከተሉት ውስጥ ከቃላዊ ግጥም የማይመደበው የትኛው ነው?

ሀ. የሰርግ ግጥም ለ. ተረት ሐ. ፉከራና ቀርቶ መ. የልመና ቃላዊ ግጥም

109. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ቃላዊ ግጥም ትክክል ያልሆነው የትኛው ነወ? ሀ. ቃላዊ

ግጥሞች የታወቀ የኔ ባይ ደራሲ የላቸውም

ለ. ቃላዊ ግጥሞች የአንድን ማህበረሰብ ባህልና ወግ ይይዛሉ

ሐ. ቃላዊ ግጥሞች በዝርው ይቀርባሉ

መ. መልሱ አልተሰጠም

110. "ዛሬ ስራ የለም__________ ወደቤት መሄድ አለብኝ።" በክፍት ቦታው ላይ የሚገባው አያያዥ ቃል የትኛው ነው?

ሀ. አለበለዚያ ለ. ስለዚህ ሐ. ይሁን እንጂ መ. እንጂ

111. "የመሠረት ልጅ **ልጨኛ** ነው።" የተሰመረበት ቃል ዓውዳዊ ፍቺ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ቁምነገረኛ ለ. ተንኮለኛ ሐ. አስቸጋሪ መ. አሽከር

112. "እንደሰባበራችሁ" የሚለው ቃል በትክክል ተነጣጥሎ የተፃፈበት አማራጭ የትኛው ነው? ሀ. አንደ-ሰባበረ-ኣችሁ

ሐ. እንደ-ሰ-ባ-በረ-ኣችሁ

ለ. እ-ንደ-ሰባበረ-ኣችሁ መ. እንደ-ሰባበረ-ኣ-ችሁ

113. ከሚከተሉት ውስጥ ብዛትን አመልካች ቅጥያን የያዘው አማራጭ የቱ ነው?

ሀ. ከመጣ ለ. ሴቶች ሐ. ሄደች መ. መፀሀፍህ

114. ከሚከተሉት ውስጥ ባለቤትን አመልካች ምዕላድ (ቅጥያ) የያዘው ቃል የቱ ነው?

ሀ. ደብተሬ ለ. ሰባበረ ሐ. የእኔ መ. ፈለጋችሁ

115. ከሚከተሉት ውስጥ ሲጠብቅ እና ሲላላ ሁለት ፍቺ የሚይዘው ቃል የትኛው ነው?

ሀ. መላ ለ. ልረዳ ሐ. ዋና መ. ሁሉም መልሶች ናቸው።

**መመሪያ ስድስት፡- <u>ከጥያቄ ቁጥር 116-120 ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ግጥም ላይ የተሐሠረቱ ናቸው። ግጥሙን ካነበባችሁ በኋላ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ</u>።**

## <u>እብሪት ሲጥለው</u>

ዕብሪት ልቡ ሲያብጥ ቢልቅ ከተራራ፣

__________________ ባንገት ቢንጠራራ፣ ብልህ

ነው እየሱስ ቃል አልተነፈሰም፣ ከዕብሪቱም ጋራ

ሽቅብ አልተነፈሰም፣ በትሁት መንፈሱ ዝቅ ዝቅ

አለና፣

ከስሩ ዘርጥጦ ጣለው ከጎዳና።

116. ግጥሙ በስንት ስንኝ እና ሀረግ ተዋቀረ በቅደም ተከተላቸው መሠረት ትክክለኛው መልስ የቱ ነው? ሀ. 6፣11 ለ. 11፣6

ሐ. 6፣12 መ. 12፣6

117. የግጥሙ ሦስተኛ ስንኝ መድረሻ ሀረግ የቱ ነው?

ሀ. ሽቅብ አልተነፍስም ለ. ቃል አልተነፈሰም ሐ. ብልህ ነው እየሁስ መ.ባንገት ቢንጠራራ

118. በግጥሙ ሁለተኛ ስንኝ ክፍት ቦታውን በመተካት የሚገባው ሐረግ እና ስንኙን ሙሉ መልዕክት የሚሰጠው ሐረግ የቱ ነው?

ሀ. ከመሬት ተነስቶ ለ. በምላስ ደንፍቶ ሐ. ሳይኖረው አጊንቶ መ.እያለው ሳይኖረው

119. የግጥሙ ቤት መድፊያ ፊደል (ሆሄ) የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ራ ለ. ም ሐ.ና መ. ሀ እና ለ መልሶች ናቸው፡፡

120. ግጥሙ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልክት የያዘው አማራጭ የትኛው ነው? ሀ. ከፍ ከፍ ማለት ሁሌም ከፍ ያደርጋል።

ለ. እብሪትና ድንፋታ የሠው ፀባይ ናቸው። ሐ. የሚያወራ ሰው ሁሌም ይከበራል።

መ. ትህትና እና ዝቅ ዝቅ ማለት ቀን ጠብቆ ከፍ ያደርጋል።

**መመሪያ ሰባት፡- <u>ከጥያቄ 121 — 130 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች ቀጥሎ የቀረበው ምንባብ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልስ ምረጡ</u>፡፡**

## <u>የአድዋ ጦርነት ፍፃሜ</u>

የአድዋ ጦርነት በ1888 ዓ.ም በየካቲት 23 እሁድ ቀን ጦርነት ተጀመረ፡፡ ወዲያው የኢጣሊያ የጦር አዛዥ ያገር ተወላጅን ጦር እፊት አስቀድሞ ሲዋጋ በኋላ የራስ መንገሻ እና የራስ ሚካኤል የዋግ ሥዩም ጓንጉል ወታደሮች ከበው በጥይት ስለቆሏው ይበልጦቹ እጦርነት ላይ ሞቱ። ጄኔራል አርሞንዲ ሰራዊት በሽሽት እየሄዱ ተደባለቁ።

የኢትዮጵያ የጦር ሰራዊትም እያቅራራና እየፎከረ ወደፊት አልፎ ጎስሶ ከሚባለው ጉብታ ላይ ደርሶ እንደና ተጋጠማቸው። በዚህ ጊዜ ጀገናው ፊታውራሪ ገበየሁ ከሰራዊታቸው ተለይተው እጠላት መካከል ገብተው ከቀኛዝማች ታፈሰ ጋር እየፎከሩ የጠላትን አንገት በጎራዴ ሲቆርጡ በጥይት ተመትተው ወደቁ፡፡

ንጉስ አጼ ምኒሊክ የጦር ወታደራቸውን በሚያበረታታ ቃል ሲያደፋፍሩ እንዲሁም እቴጌ ጣይቱ እንደ ወንድ በጦርቱ መካከል እየተላለፉ የቆሰለውን ሲያነሰ ፣ ለተጠማው መጠጥ ለተራበው ምግብ ሲሰጡ ዋሉ። እነ ሊቀመኳስ አባተ እነራስ አሉላ እነ በጅሮንድ ባልቻ እነደጃች ባሻህ አቦዬና የቀሩትም የጥንት ወታደሮች በመድፍና በጠመንጃ በጀግንነት ሲዋጉ የጠመንጃውና የመድፍ ጩኸት ከልክ ያለፈ ነበር።

የኢጣሊያንም ወታደር ከበው የተፏከሩ በጥይት እና በጎራዴ ሲደበድቡት የኢጣሊያ ጦር በጀግንነት አራት ሰዓት ከተዋጋ በኋላ ሽሽት ጀመረ። በዚህ ጊዜ ኢትዮጵያዊያን እየተከተሉ ሲወጉት አዝማቹ ጄኔራል አልበርቲኑ ተቀምጦበት የነበረው በቅሎ ተመትሮ ወደቀ ፤ ኢትዮጵያዊያ ደርሰው ጄኔራሉን ማረኩት።

የአንደኛው ክፍለ ጦር አዛዥ ተማርኮ በጭራሽ ሰራዊት ከጠፋ በኋላ በሁለተኛው ክፍለ ጦር ሰራዊት ራአዮ ከሚባለው ስፍራ ላይ ሆኖ ካራት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ የሶስተኛው ክፍል የጄኔራል ኤሌናን ጦር ጨምሮ ተዋግቶ በመጨረሻ የቶር አዛዡ ጄኔራል አርሞንዲ እዚያው እጦነቱ ላይ ሞቶ ተገኙ፡፡ ከዚህም በኋላ በመጨረሻው የኢጣሊያ ጦር በተለይ ማርያም ሸዊት ከሚባው ስፍራ ላይ ተጋጥሞ ከቀድው የበለጠ ጦርነተ ተደረገ፡፡ ይልቁንም የመጨረሻው ድል የሚፈጸምበት ለመሆን የሁለቱም የጦር ሰራዊት ተደባልቅ በጨበጣ በሚዋጉበት ጊዜ በጨበጣ በሚደረግ ዘመቻ ከኢጣሊያች ይልቅ አትዮጵያዊያን በጎራዴ አነዛዘር የቀለጠፉ ነበሩ፡፡

በዚህም ጊዜ ኢጣሊያኖች ጎሚሶቹ ሲሞቱ የተቀሩ ደግሞ ወደ ኢትዮጵያዊያ ደግነው ይተኩሱበት የነበረው ብረት አፈሙዙን ጨብጠው

121. እቴጌ ጣይቱ በጦርነት ወቅት ያበረከቱት አስተዋፅኦ የተጠቀሰው በስንተኛው አንቀፅ ነው? ሀ. አንድ ለ. ሶስት ሐ. ሁለት መ. አራት

122. በመጀመሪያው አንቀፅ ጦሩ ያልተነካበት ጄኔራል ማን ነው?

ሀ. ራስ ሚካኤል ሐ. ጄኔራል አርሞንዲ

ለ. ራስ መንገሻ መ. ጄኔራል አልበርቶኒ

123. በጥይት ተመተው ወደቁ የተባሉት እነማን ናቸው?

ሀ. ፊት አውራሪ ገበየሁ ሐ. በጅሮንድ ባልቻ

ለ. ሥዩም ጓጉል መ. ደጃች በሻህ አቦዬ

124. በጀግንነት ለአራት ሠዓት ያህል የተዋጋው ማነው?

ሀ. የኢትዮጵያ ወታደር ሐ. ጄኔራል አልበርቶኒ

ለ. የኢጣሊያ ሰራዊት መ. አጼ ሚኒሊክ

125. የአድዋጦርነት ፍጻሜ መቼ ነበር?

ሀ. የካቲት 23 1988 ዓ.ም ሐ. የካቲት 23 1888 ዓ.ም

ለ. የካቲት 23 1986 ዓ.ም መ. የካቲት 27 1888 ዓ.ም

126. በጥይት **<u>ስለቆሏቸው</u>** ሲል

ሀ. ስላበሰሏቸው ለ. ስለደበደቧቸው ሐ. ስላመሷቸው መ. ሁሉም

127. ከአራት እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ውጊያ የተካሄደበት ቦታ የት ነው?

ሀ. ጎስሶ ለ. ርአዬ ሐ. ውጫሌ መ. መልሱ አለተሰጠም

128. የሶተኛው ክፍለ አዛዥ ጄኔራል የነበሩት ማንናቸው?

ሀ. ጄኔራል አሌናን ሐ. ጄኔራል አልቤርቶኒ

ለ. ጄኔራል አርሞነዲ መ. ሁሉም መልስ ነው

129. "በጅሮንድ" ማለት

ሀ. የግለሰብ ስም ነው　　　　ሐ. የመሳሪያ ስም ነው

ለ. የማዕረግ ስም ነው　　　　መ. የአገር ስም ነው

130. "በጨለማ" በሚደረገው ውጊያ ላይ ሲል

ሀ. በሽምቅ　　ለ. በፊት ለፊት　　ሐ. በእርዳታ　　መ. በውክልና

**መመሪያ ስምንት፡- ከጥያቄ 131 -163 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳዱ ጥያቄ ከረቡት አማራጭ መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።**

131. ጓደኛውን ባገኝ ጊዜ <u>ልቡ ወከክ አለ</u>። የተሰመረበት ፈሊጣዊ አነጋገር ፍቺ ከሚከተሉት የትኛው ነው?

ሀ. ፀጥ አለ　　ለ. ደከመ　　ሐ. ተደሰቱ　　መ. ተተረተረ

132. "እህል ውሀ ቀመሥ" ለሚለው አገላለፅ ፍቺ የሚሆነው?

ሀ. አፉን አሟሸ　　ለ. አፉን አበሰ　　ሐ. አፉን አጣፈጠ　　መ. አፉን አጣጠመ

133. "ጥርስ ገባ" ለሚለው አገላለፅ ፍቺ የሚሆነው?

ሀ. ተሞሸረ　　ለ. ተጋበዘ　　ሐ. ተኩራራ　　መ. ተጠላ

134. "እጅ አጠረው" ለሚለው አገላለፅ ፍቺ የሚሆነው

ሀ. ገንዘብ አገኘ　　ለ. ደላው　　ሐ. ተቸገረ　　መ. ተትረፈረፈ

135. "ቅቤ አንጓች" ለሚለው አገላለፅ ፍቺ የሚሆነው?

ሀ. አድር ባጣ　　ለ. አዛኝ　　ሐ. ተወዳጅ　　መ. ቸር

136. በቃለ መጠይቅ ዝግጅት ከሚከተሉት መካከል ቀዳሚ የሆነው የቱ ነው? ሀ. ጥያቄ ማዘጋጀት　　　　ሐ. ቀጠሮ መያዝ

ለ. ተጠያቂውን ማመስገን　　　　መ. ደብዳቤ መፃፍ

137. ከሚከተሉት የድርሰት ክፍሎች መካከል በብዙ ዓ.ነገሮች ይዋቀራል።

ሀ. መግቢያ　　ለ. ሀተታ　　ሐ. መደምደሚያ　　መ. መቋጨያ

138. የቃላት ምርጫ የበለጠ ስልት የሚታይበት የትኛው የድርሰት አይነት ነው?

ሀ. ስዕላዊ　　ለ. አስረጂ　　ሐ. አመዛዛኝ　　መ. ተራኪ

139. ሰው በገንዘብ እያታለለ የሚገድል ከሚከተሉት አማራጮች በየትኛው ይጠራል?

ሀ. አሳስቶ አራጅ　　ለ. አዘናግቶ አራጅ　　ሐ. አድብቶ አራጅ　　መ. አስብቶ አራጅ

140. "መናገር ቻለ ወይም ጀመረ" ለሚለው አገላለፅ አቻ ትርጉም ያለው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

ሀ. አፋን አናገረ ለ. አፋን አሾለ ሐ. አፋን ፈታ መ. አፋን አሳየ

141. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ብዛትን የሚያመለክት ቅጥያ ያልያዘው የትኛው ነው?

ሀ. ከብቶቻቸው ለ. መሰቦቻቸው ሐ. ጎረቤቶቻቸው መ. ነገረቻቸው

142. ከሚከተሉት ቃላት መካከል የተለየው የትኛው ነው?

ሀ. ሌጣ ለ. ጥንድ ሐ. ብቸኛ መ. ነጠላ

143. **ወስፌ** ለሚለው ቃል ፍካሬያዊ ፍቺ የሚሆነው የቱ ነው?

ሀ. መስፊያ ለ. ተንኮለኛ ሐ. ሆዳም መ. ቀጭኔ

144. አንድ አንቀፅ መሪ ሃሳብ የሚኘው

ሀ. በመጀመሪያ ለ. መሃከል ሐ. መጨረሻ መ. ሁሉም

145. ያ ቤት ጥሩ ሆኖ ቀለም ተቀብቷል። በዚህ ዓ.ነገር ውስጥ አመልካች ተውላጠ ስሙ። ሀ. ቤት ለ. ጥሩ

ሐ. ያ መ. እኔ

146. ወደፊት ለመሄድ እንሩጥ ወደኋላ፣

እንደ ግንድ እንደ ዛፍ ዋርካ እንሁን አለ። ይህ ግጥም በምን አይነት ዘይቤ ነው የተኳለው? ሀ. እንቶኔ ለ. አያዎ ሐ. አነፃፃሪ መ. ምጸት

147. "አዛባ" ለሚለው ቃል ጠብቆ ሲነበብ የሚሰጠው ትርጉም __________________ ነው።

ሀ. ረኸጥ ለ. የላቀጠ ጭቃ ሐ. የላቀጠ እበት መ. ፍርድ ገመደለ

148. "እሳት ይምታው" ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. መጥፎ ያጋጥመው ለ. ማድረቅ ሐ. ይብሰል መ. ችግር ይጥበሰው

149. የሚከተሉት ተዘበራርቀው የተቀመነጡ ያክርክር ዝግጅትና አቀራብ ተግባ ትክክለኛ ቅደም ተከተል የትኛው ነው?

1. ረጋ ብሎ መከራከር
2. አድማጮችን ማመስገን
3. መረጃዎችን ማሰባሰብ
4. ልምምድ ማድረግ

ሀ. 1 ፣ 2 ፣ 4 ፣ 3 ሐ. 4 ፣ 2 ፣ 3 ፣ 1

ለ. 4 ፣ 3 ፣ 1 ፣ 2 መ. 3 ፣ 4 ፣ 1 ፣ 2

150. ዶ/ር **ከበደ** ትናንት መጣ። በዚህ ዓ.ነገር የተሰመረበት ስም በየትኛው ተውላጠ ስም ሊተካ ይችላል? ሀ. እነርሱ ለ. እናንተ

ሐ. እኛ መ. እሱ

151. ጣይቱ **<u>ሁልጊዜ</u>** ለስላሳ ትጠጣለች። በዓ.ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ከየትኛው የቃል ክፍል ይመደባል?

ሀ. ተውሳከ ግስ ለ. ተውላጠ ስምሐ. ግስ መ. ስም

152. ______________ ይህ ስልት መንስኤና ውጤትን በማስተሳሰር አንቀፅ የሚፃፍበት ነው። ሀ. ገለፃ ለ. ምክንያና ውጤት ሐ. ምስያ መ. አስረጂ

153. ሙትን መውቀስ________________። የተጓደለው ምሳሌያዊ አነጋገር ሊያሟላ የሚችለው ከሚከተሉት አማራጮች የትኛው ነው።

ሀ. ውሃ ማፍሰስ ለ. ራስ ማሳነስ ሐ. ድንጋይ መንከስ መ. ደግሞ ማልቀስ

154. የአህ ቀበጥ________________። የተጓደለው ምሳያዊ አነጋገር ሊያሟላ የሚችለው ከሚከተሉት አማራጭ የትኛው ነው።

ሀ. ከላም ይጠባል ለ. ከፈረስ ይጠባል ሐ. ከዝሆን ይጠባል መ. ከጅብ ይጠባል

155. ከሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች መካከል ወሬኝነትን የሚኮንን የትኛው ነው? ሀ. ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው

ሐ. ምዘኛ የኑሮ መጋኛ

ለ. ምክር የብልህ ሀብት የግልህ

መ. ዘመድን የማ ራሱ ገማ

156. የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሊቪዥን ድርጅት በምህጻረ ቃል ሲጻፍ የቱ ነው?

ሀ. የኢ.ሬ.ቴ.ድ ለ. ኢ.ፌ.ቴ.ድ ሐ. ኢ.ሬ.ቴ.ድር መ. ኢ.ቴ.ድ

157. **<u>የልጅ አስተሳሰብ</u>** በጣም ይገርማል በሚለው ዓ.ነገር የተሰመረበት ምን አይነት ሀረግ ነው? ሀ. ቅፅላዊ ሀረግ

ሐ. ስማዊ ሀረግ

ለ. መስተዋድዳዊ ሀረግ

መ. ግሳዊ ሀረግ

158. ገረፈቻቸው የሚለው ቃል ውስጥ ስንት ምዕላዶች እንደያዘ የሚያመለክተው የትኛው ነው? ሀ. ሁለት ለ. አንድ ሐ. ሶስት መ. አራት

159. ልጅ ፈተናውን አለፈ። በዚህ ዓ.ነገር ተሳቢ ቃል የቱ ነው?

ሀ. ልጅ ለ. ፈተናውን ሐ. አለፈ መ. ልጅ ፈተናውን

160. ከሚከተሉት የንባብ አይቶች እንደ ልብ ወለድ ያሉ ፅሁፎችን ለማንበብ የሚጠቅም ነው? ሀ. የገረፍታ ንባብ ሐ. ሰፊ ንባብ (ፍጥነት)

ለ. በአሰሳ ማንበብ

መ. የዝግታ ንባብ

161. ቀጥሎ የቀረበው ሥነ-ቃል (ግጥም) ከየትኛው ይመደባል? ጡረው

ጡረው አማችህን ፣

ከዚች ቆንጆ ያጋባህን።

ሀ. የሙገሳ ለ. የእርሻ ሐ. የሀዘን መ. የሰርግ

162. የተለያ ምጮች መረጃ ለማግኘት የምንጠቀምባቸው ክሂሎች የትኞ ናቸው? ሀ. መጻፍና መናገር ሐ. ማንበብና መናገር

ለ. ማንበብና ማዳመጥ መ. መጻፍና ማበብ

**መመሪያ ዘጠኝ፡- ከተራ ቁጥር 45—49 ለቀረቡት ቃላት በፍቺ ተመሳሳይ ይሆናሉ ተብለው ከተሰጡት አማራጮጭ መካከል ይበልጥ የሚስማማውን ምረጥ፡፡**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 163. ህልውና | ሀ. ምኞት | ለ. መኖር | ሐ. ሞት | መ. ህመም |
| 164. አልባሌ | ሀ. ትንሽ | ለ. ከሀዲ | ሐ. ሽብቀኛ | መ. መናኛ |
| 165. ፍትህ | ሀ. ፍርድ | ለ. ፍቺ | ሐ. ወንጀል | መ. ደስታ |
| 166. ተናኘ | ሀ. አወከ | ለ. መረዘ | ሐ. ተሰራጨ | መ. ተዋበ |
| 167. ስርቅታ | ሀ. ምንተፋ | ለ. ትንታ | ሐ. ህቅታ | መ. ኩርፍታ |

**መመሪያ አስር፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሚከተለው አንድ አንቀፅ ድርሰት ከላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መልሶች መካከል ትክክለኛው ምረጡ፡፡**

ከሙሽሮቹ ፊት ለፊት መሐል ስፍራ የሴቶች አንገትና ወገብ ፣ የወንዶች ትከሻና ደረት የሚለካበት መድረክ ሆኖ ባሕላዊ አስክስታና ጭፈና ቀልጦበታል።

የሚያጨበጭበው ዜማውን የሚቀበለውና የሚያደምቀው የሚወዛወዘው ሁሉ ፊቱ ላይ ሞቅ ያለ የደስታ ፈገግታ ይታይበታል፡፡ ሁሉም ወዛም ሆኗል____________________ አመዳሙን ጨምሮ፡፡ ሁሉም ሳቂታና ጥርሶቹን ያሰጣ ሆኗል ____________________________________ ኮስታራውንም ጨምሮ፡፡

168. የዚህ አንቀፅ ድባብ ምንድን ነው?

ሀ. የግብዣ ለ. የጭፈራ ሐ. የሰርግ መ. ቀውጦታል

169. "ቀልጦበታል" የሚለው ቃል ከአገባቡ የሚሰጠው ትርጉም ከሚከተሉት የትኛው ነው? ሀ. ወዝቶበታል ለ. ደምቆበታልሐ. ፈሶበታል መ. ቀውጦታል

170. በአንቀጹ ሁለተኛ ዓ.ነገር ውስጥ የጎደለው ሥርዓተ ነጥብ ከሚከተሉት የትኛው ነው?

ሀ. ፤ ለ. ፡ ሐ. ። መ. ፣

171. በአንቀፁ የመጨረሻ ሁለት ዓ.ነገሮች ውስጥ የባዶ ቦታ ምልክት ባለባቸው ቦታዎች ውስጥ መግባት ያለበት ሥርዓተ ነጥብ ከሚከተሉት የትኛው ነው?

ሀ. ፣ ለ. ። ሐ. ፤ መ. …….

172. ከላይ የቀረበው አንቀፅ የተፃፈበት የድርሰት አይነት ከሚከተሉት የትኛው ነው?

ሀ. ገላጭ ለ. አመዛዛኝ ሐ. ቅስቀሳ መ. ትረካ

**መመሪያ አስራአንድ:- <u>ከታች የቀረበውን ግጥም በትኩረት ካነበባችሁ በኋላ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ተገቢው መልስ ምረጡ</u>::**

**<u>ግጥም አንድ</u>**

እንደ ዳመነ ጓል ታይቶ እንደሚበተን

የአንድ አፍታ ክስተት ነው ህይወት ሲተነተን በዓለም ብዙ

ሆኗል አልፏል ተከውኖ

አሻራ እየተወ "ነው ነበር"ን ሁኖ በጊዜ ስንክሳር

ታሪክ ሆነ ፋና

መልካም ሥራ አይሞትም ሟች ይሸኝና ጊዜ

ሳይሽራቸው ሳይገታቸው ድንበር ታሪክ ሲሆኑ

ክብር ሀቅና ቁምነገር ይቺን ጥቂት ነገር መስራት

እያቃተው ከንቱ ይቀራል ሰው መታሰቢያ

ሳይተው

***ምንጭ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር (1999) የዘመን ቀለማት***

173. ከላይ የተጻፈውን ግጥም ከሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች በየትኛው ማጠቃለል ይቻላል? ሀ. ለስሟ መጠሪያ ቁና ሰፋች፡፡

ለ. ስም ከመቃብር በላይ ይውላል፡፡

ሐ. ጊዜ ሲያመልጥ ራስ ሲመለጥ አይታወቅም፡፡ መ. ሳይቀር ሞቴ ክፉ መስራቴ፡፡

174. በግጥሙ ውስጥ ስንት ስንኞች አሉ?

ሀ. 10 ለ. 5 ሐ. 20 መ. 15

175. የግጥሙ አራተኛ ስንኝ መነሻ ሀረግ ከሚከተሉት ግጥሞች የቱ ነው? ሀ. አሻራ እየተወ ነው

ሐ. አሻራ እየተወ

ለ. "ነው" ነበር ና ሆኖ

መ. "ነበር"ን ሆኖ

176. በአራተኛው ስንኝ ውስጥ የተጠቀሱት "ነው" እና "ነበር" የሚያመለክቱት ሁሉንም ነገር በጊዜ ሂደት እንደማለፍ ነው?

ሀ. ህይወትና ለ. አሻራን ሐ. ዓለምን መ. ጊዜን

177. በግጥሙ ውስጥ ስንት መነሻ ሀረጎች አሉ?

ሀ. 10 ለ. 20 ሐ. 15 መ. 5

178. በግጥሙ ውስጥ በሳድስ ፊደል የሚጨርሱ ስንት ስንኞች አሉ?

ሀ. 2 ለ. 4 ሐ. 3 መ. 1

**መመሪያ አስራ ሁለት፦** **ከተራ ቁጥር 180- 184 ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበዉ ምንባብ ላይ የተመሰረቱ ናቸዉ፡፡ ምንባቡን በጥሞና በማንበብ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ ምረጭ፡፡**

አንድ ጅብ በሩቅ አህያ ተመለከተና ሊበላዉ ወሰነ፡፡ እየሮጠም ወደ አህያዉ ተጠጋ ጅቡን የተመለከተወ አህያም ማምለጥ እንደማይችል ተረዳ፡፡ ድንገት አንድ ብልሀት ወደ አእምሮዉ መጣለት፡፡ እያነከሰ ለመሸሽ ሞከረ፡፡ ጅቡ ይደርስበትና አህያዉን ከመዘርጠጡ በፊት፣"ምናባክ ሆነህ ነዉ የምታነክሰዉ?" ሲል ጠየቀዉ አህያም "ጌታየ! ገደል ስዘል እሾህ ወግቶኝ ነዉ፡፡ እግሬ ዉስጥ የገባዉ እሾህ በጣም መርዘኛ ነዉ፤ ልትበላኛ ከፈለክ መጀመሪያ እግሬ ዉስጥ የገባዉን እሾህ ንቀልልኝ፡፡ ምክንያቱም እሾሁ በጣም መርዘኛ ከመሆኑ የተነሳ በምትበለኝ ጊዜ ይወጋህና ይገድልሀል፡፡ የሚሻለዉ መጀመሪያ ነቅለህልኝ ብትበላኝ ነዉ፤" አለዉ፡፡

ጅቡም ምክር ስለተስማማ ከአህያዉ ሥር ቁጭ አለና እሾሁን ለማዉጣት በአፉና በምላሱ መደባበስ ጀመረ በዚህ ጊዜ አህያዉ ጅቡን በሀይለኛ እርግጫ ሲያቀምሰዉ ጥርሱ እርግፍግፍ አለ፡፡ አሁን አህያና ጅብ እኩል ሆኑ፡፡ በምኑ ይብላዉ? በዚህ ጊዜ አህያዉ በጣም ይደሰትና" በልጡ ሲያመልጥ አየኽዉ?" በማለት ሳቀበት፡፡

179. በምንባቡ ዉስጥ አህያዉ የተላበሰዉ ጠባይ ምን ነበር ?

ሀ. ሞኝ ለ. አታላይ ሐ. ብልህ መ. ስግብግብ

180. በምንባቡ ዉስጥ አኩይ ጠባይ ተላብሶ የቀረበዉ ማነዉ ?

ሀ. ጅብ ለ. እሾህ ሐ. አህያ መ. እግር

181. ምንባቡ ከየትኛዉ የሥነ ፁሁፍ ዘዉግ ይመደባል ?

ሀ. ከቀልድ ለ. ተረት ሐ. አጭር ልብወለድ መ. ከመነባንብ

182. በምንባቡ ዉስጥ "ሲያቀምሰዉ" የሚለዉ ቃል አገባባዊ ፍቺ ምንድን ነዉ ?

ሀ. ሲልሰዉ ለ. ሲያጎርሰዉ ሐ. ሲገፋዉ መ. ሲመታዉ

183. ከሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች መካከል ጅቡን በተሻለ ሁኔታ የሚገልፀዉ የትኛዉ ነዉ ?

ሀ. ጅብ እስኪነክስ ያነክስ ሐ. አያ ጅቦ ሳታማካኝ ብላኝ

ለ. ሞኝ ቢሸከም የበላ ይመስለዋል መ. ሆዱን ያለ ሆዱን ተወጋ

**መመሪያ አስራ ሶስት፦ ከተራ ቁጥር 185 - 189 ሥርዓተ ነጥብን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነዉን መልስ ምረጥ ምረጪ፡፡**

184. ምህፃረ ቃልን ለመፃፋ የምንጠቀምባቸዉ የሥርዓተ ነጥብ ምልክቶች የያዘው አማራጭ የትኛዉ ነዉ ?

ሀ. / .　　ለ. - . . .　　ሐ. .　　መ. / ,

185. -------- ኤሎሄ ---------- ኤሎሄ --------- ላማ ሰበቅስታኒ -------- ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፡፡ ለክፍት ቦታዎቹ አስፈላጊ የሆኑት ሥርዓተ ነጥቦች እንደ ቅደም ተከተላቸዉ የትኞቹ ናቸዉ ?

ሀ. " ! ! ! "　　ለ. " " ! ! ? "　　ሐ. " ፣ ፤ ! ?　　መ. " " ! ! ? ፡፡

186. አግዚኦ ----የሰዉ ያለህ ---- ድረሱልኝ ----- ከሚሉት አገላለጾች ጋር የሚጎዳኘዉ ሥርዓተ ነጥብ ---------------ነዉ ?

ሀ. ትዕምርተ ስላቅ　　ለ. ትዕምርተ አንክሮ　　ሐ. ትዕምርተ ጥያቄ　　መ. አራት ነጥብ

187. የእኔ ግንድ አግር ------- የእኔ ዱባ ------- የእኔ ድብኝት ------ ለሚሉት ገለፃዎች ይበልጥ የሚስማማዉ ሥርዓተ ትምህርት ------------------ ነዉ ?

ሀ. ትዕምርተ ጥያቄ　　ለ. ትዕምርተ አንክሮ　　ሐ. ትዕምርተ ስላቅ　　መ. አራት ነጥብ

188. ሀገሬ ተባብራ ካልረገጠች ርካብ
ነገራችን ሁሉ የእምቧይ ካብ የእምቧይ ካብ
በግጥሙ ቤት መምቻና ቤት መድፊያ ላይ የሚገቡት ሥርዓተ ነጥቦች፤

ሀ. ፣ እና ፤　　ለ. ፣ እና ¡　　ሐ. ፣ እና !　　መ. ፣ እና ፡፡

**መመሪያ አስራ አራት፦ ከተራ ቁጥር 190 - 194 ድረስ አምስት ያልተሟሉ ምሳሊያዊ አነጋገሮች ቀርበዋል፡፡ እያንዳንዱን ምሳሌያዊ ንግግር ያሟላሉ ተብለዉ ከታሰቡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነዉን መልስ ምረጥ/ምረጪ፡፡**

189. ጉንፋን ቢያኮሩት ------------------------------ ፡፡

ሀ. ወረርሽኝ ይሆናል　　ለ. አመት ያስተኛል　　ሐ. ፈዉስ ያስገኛል　　መ. ገመምተኛ ያደርጋል

190. ሞኝ የዕለቱን---------------------------------፡፡

ሀ. ብልጥ የወደፊቱን　　ሐ. ብልህ የአመቱን

ለ. ዓዋቂ የትናንቱን　　መ. ለጋሽ ከረጢቱን

191. -----------------አመሏን አትረሳ፡፡

ሀ. አሮጊት መንኩሳ ለ. ድመት መንኩሳ ሐ. አይጥ መንኩሳ መ. ጥንቸል መንኩሳ

192. አበዉ ሲመስሉ ማምሻም------------------------------- ይላሉ፡፡

ሀ. እረፍት ነዉ ለ. መዝናኛ ነዉ ሐ. ኑሮ ነዉ መ. እድሜ ነዉ

193. የሌባን ጠበቃ--------------------------------፡፡

ሀ. ማቅረብ ለአለቃ ለ. መግረፍ በጨረቃ ሐ. ግረፍ በፈረቃ መ. አደባልቀህ ዉቃ

## መመሪያ አስራ አምስት፦ ከጥያቄ 195 - 227 የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ምረጭ፡፡

194. ክንዴን ሳልንተራስ ማንም የሚደፍርህ የለም፡፡ ለሚለዉ ፈሊጣዊ አነጋገር ፍች የሚሆነዉ የትኛዉ ነዉ?

ሀ. ሳልሞት ለ. ሳላንቀሳፋ ሐ. በደዌ ሳልያዝ መ. የአልጋ ቁራኛ ሳልሆን

195. ከሚከተሉት ዉስጥ አንድ ብቻ ፍች ያለዉ ቃል የትኛዉ ነዉ ?

ሀ. ሰለለ ለ. አዛባ ሐ. ነገረ መ. መተረ

196. መልስ ሰጪዉ ያቀረበዉ ምን አይነት ሐሳብ ነዉ? ጠያቂ -
የደን መጨፍጨፍ ምንን ያስከትላል መላሽ - ድርቅን
ይጋብዛል

ሀ. እርግጠኛ ለ. የግል አስተያየት ሐ. ሉታዊ መ. አጠራጣሪ

197. ተጋባዦቹ የክት ልብሳቸዉን ለብሰዋል፡፡ የክት ልብስ የሚለዉ ተቃራኒ ፍቺ ምን ይሆናል? ሀ. የአዉዳመት ለ. የፀሎት ሐ. የዘወትር መ. የሰርግ

198. አዳኙ ጦሩን ------- ጥቅጥቅ ወዳለዉ ጫካ ገባ፡፡ ባዶ ቦታዉን የሚያሟላዉ ቃል የትኛዉ ነዉ? ሀ. እየቀሰረ ለ. እየወደረ ሐ. እያነጣጠረ መ. እየሰበቀ

199. "ወልዳችሁ ሳሙ ፤ ዘርታችሁ ቃሙ" የሚለዉ አባባል ከሚከተሉት ዉስጥ የትኛዉን የሚገልፅ ነዉ?

ሀ. ሙገሳን ለ. ትጋትን ሐ. ምክርን መ. ምርቃትን

200. ለደስታ ለሀብታም ይጨቀያል ደጁ፣ ለአቶ
መከራማ ጥቂት ነዉ ወዳጁ፡፡ የቅኔዉ ሕብረ
ቃል የትኛዉ ነዉ ?

ሀ. ደስታ ለ. መከራማ ሐ. ጥቂት መ. ወዳጁ

201. ሽቶዉ ያዉዳል ፤ ጉራማይሌ የተነቀሱት ጥርሶቿ እንደ እንቁ ይበራሉ ፤ ከደረቱ ከፍት የሆነ ጥቁር ሹራብ ጣል አድርጋለች ፤ ያንገት ጌጥዋ ደረትዋ ላይ አረፍ ብሏል። ይህ ፁሁፍ የቀረበበት የድርሰት አይነት መካከል በየትኛዉ ስልት የተፃፈ ነዉ?

ሀ. አከራካሪ ለ. ገላጭ ሐ. ተራኪ መ. ስዕላዊ

202. ልጇቱ ሳላስብ እያሰብኩ አለች። ይህ ዓ/ነገር የቀረበበት የዘይቤ አይነት የቱ ነዉ ?

ሀ. እንቶኔ ለ. ምፀት ሐ. አያዋ መ. ሠወኛ

203. በራፉም ይከፈት ሁሉም ይሰናዳ፣ ልክ የለዉም

አሉ ለዚህ ቤት እንግዳ።

ከሚከተሉት የሥነ ቃል ዘርፎች መካከል ለየትኛዉ ተስማሚ ነዉ?

ሀ. የሙገሳ ለ. የሠርግ ሐ. የሀዘን መ. የእርሻ

204. ከሚከተሉት የድርሰት ክፍሎች መካከል በብዙ ዓ/ነገሮች የሚዋቀረዉ የቱ ነዉ?

ሀ. መግቢያ ለ. መደምደሚያ ሐ. መቋጪያ መ. ሀተታ

205. ከሚከተሉት መካከል በእዉነት ላይ ያልተመሰረተዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ደብዳቤ ለ. ማስታወቂያ ሐ. ልብወለድ መ. የሕይወት ታሪክ

206. "ነት" የሚለዉ ቅጥያ ተጨምሮበት የሚታየዉ የትኛዉ ቃል ላይ ነዉ?

ሀ. መቀነት ለ. ልጅነት ሐ. ግነት መ. እዉነት

207. ረጅምና ቀጭኑ ልጅ እየሮጠ መጣ። በዚህ ዓ/ነገር ዉስጥ የሚገኙት ቅፅሎች የትኞቹ ናቸዉ ?

ሀ. ረጅሙና ቀጭኑ ሐ. ቀጭኑና ልጁ

ለ. እየሮጠ መጣ መ. ረጅሙና ልጅ

208. እንቅብ የሚለዉ ቃል ከየትኛዉ የስም አይነት ይመደባል ?

ሀ. የወል ስም ሐ. የቁሣቁሥ መጠሪያ ስም

ለ. የተፅዉኦ ስም መ. የረቂቅ ነገሮች መጠሪያ ስም

209. ከሚከተሉት ዓ/ነገሮች ትዕምርተ አንክሮ መጨረሻ ላይ የሚጠቀመዉ የቱ ነዉ? ሀ. ሀተታ ዓ/ነገር

ሐ. ትዕዛዛዊ ዓ/ነገር

ለ. ጥያቄያዊ ዓ/ነገር መ. አጋናኝ ዓ/ነገር

210. "ልጆቹ በየጊዜዉ ገላቸዉ ስለሚታጠብ ጤንነታቸው በሚገባ ተጠብቋል ለማለት ይቻላል።" በዚህ ዓ/ነገር የሚታየዉ ስህተት ----------- ነዉ ?

ሀ. የቁጥር ለ. የጾታ ሐ. የባለቤት መ. የጊዜ

211. የፈተናዉ ጊዜ ደርሷል። ------------------ አላጠናችም። ባዶ ቦታዉን የሚያሟላዉ የቱ ነዉ ?

ሀ. ስለዚህ ለ. እንዲያዉም ሐ. ይሁን እንጂ መ. በአንፃሩ

212. አንድ አንባቢ አንድን ፁሁፍ በመመርመር ፣ በፁሁፉ ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎች ለመመለስ ከሚከተሉት የንባብ አይነቶች የትኛዉን መጠቀም አለበት ?

ሀ. የፍጥነት ንባብ ለ. የገረፍታ ንባብ ሐ. የአሠሳ ንባብ መ. የዝግታ ንባብ

213. ከሚከተሉት መካከል የክርክር ዝግጅት መመሪያ የሆነዉ የቱ ነዉ ?

ሀ. ልምምድ ማድረግ ሐ. ሁሉንም ነገር አለማንበብ

ለ. ርዕስን ማስተዋወቅ መ. ምስጋና ማቅራብ

214. ሐሴት ለሚለዉ ቃል ተቃራኒ የሚሆነዉ የቱ ነዉ ?

ሀ. ደስታ ለ. ፅልመት ሐ. ፍስሀ መ. ፍካት

215. ከሚከተሉት ቃላት መካከል የመጀመሪያ የሚለው ፍቺ የሚሰጠዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ቤዛ ለ. ቀየ ሐ. ጋለሞታ መ. በኩር

216. የአባቱ መሞት --------------- በጣት ነገሩት። ባዶ ቦታዉ ላይ የሚገባዉ ቃል የቱ ነዉ? ሀ. መርዶ ለ. ሀሴት

ሐ. መታወክ መ. ግፍ

217. "ነጋሪት ተጎሰመ ፣ ከበሮ ተደለቀ" ከተባለ " ማሲንቆ ----------- ዳንኪራ------------------------------------------ ይባላል።"

ሀ. ተመታ ፣ ተረገጠ ሐ. ተጫወተ ፣ ተወዛወዘ

ለ. ተረገጠ ፣ ተመታ መ. ተገዘገዘ ፣ ተነፋ

218. "ወደቀ" "ብሎ" "ተነሳ" ካለ "አያሌ" ብሎ ምን ይላል?

ሀ. ብዙ ለ. ሩቅ ሐ. ጥቂት መ. ቅርብ

219. ኮኮብ ለሚለዉ ቃል ፍቺ የሚሆነዉ ---------------- ነዉ ?

ሀ. ዋና ለ. በሠማይ የሚታይ ሐ. ተስፋ መ. ሠማይ

220. አንደበተ ርቱዕነት ከቋንቋ ክሂሎች መካከል ከየትኛዉ ጋር አብሮ ይሄዳል ?

ሀ. ከመፃፍ ለ. ከማንበብ ሐ. ከማዳመጥ መ. ከመናገር

221. "ሳያስበዉ ተናጋሪ" የሚለዉ ሐሳብ ከሚከተሉት ከየትኛዉ አማራጭ ጋር ይመሳሰላል ?

ሀ. ምላሱን ጎለጎለ ለ. ምላስ አወጣ ሐ. ምላሱን አሾለ መ. ምላሱን አዳጠዉ

222. ገለል በሉለት አንደዜ ለሱ፣

ግልግል ያዉቃል ከነፈረሱ። ይህ ግጥም ከየትኛዉ ቃላዊ ግጥም ይመደባል?

ሀ. የሠርግ ግጥም ለ. የእርሻ ግጥም ሐ. የፉከራ ግጥም መ. የልመና ግጥም

223. ________________________ ጭንቀትና ስቃይ የገነነበት የተዉኔት አይነት ነዉ?

ሀ. ኮሜዲ ለ. ቧልታይ ሐ. ድንቃይ መ. ትራጀዲ

**መመሪያ አስራ ስድስት፦ ከተራ ቁጥር 228 - 234 ለቀረቡት ቃላት በፍቺ ተመሣሣይ የሚሆነዉን ምረጡ፡፡**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 224. ዘመመ | ሀ. ወደቀ | ለ. አዘነበለ | ሐ. ተጣመመ | መ. ቆዘመ |
| 225. ሠመረ | ሀ. ቀጥ አለ | ለ. ጠነከረ | ሐ. ቆመ | መ. ተሳካ |
| 226. ደራ | ሀ. ሰፋ | ለ. ተስማማ | ሐ. ዳበረ | መ. ሞቀ |
| 227. አሉባልታ | ሀ. ሹክሹክታ | ለ. ጭምጭምታ | ሐ. ሃሜት | መ. ነገር |
| 228. ጎባን | ሀ. አያት | ለ. ጣዉንት | ሐ. ዉሽማ | መ. ምራት |
| 229. ዘከረ | ሀ. አስተናገደ | ለ. አስታመመ | ሐ. አስታወሰ | መ. አከረረ |
| 230. ባዝራ | ሀ. ብዙ | ለ. ሴት ፈረስ | ሐ. ትንሽ | መ. ባእድ |

**መመሪያ አስራ ሰባት፦ ከጥያቄ 235 - 239 ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበዉ ግጥም ላይ የተመሰረቱ ናቸዉ፡፡ ግጥሙን በትኩረት ካነበባችሁ በኂላ ለእያንዳንድ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ተገቢዉን መልስ ስጡ፡፡**

ፈልቀሽ የተገኘሽ ከሹበርት ራስ ከቤቶቨን ናላ
ከሞዛርት መንፈስ ከሾፐን ትካዜ ከያሬድ
ልቦና መዓዛ የሞላሽ የብስጭት ቃና ረቂቅ
ድምፅ ሆይ ዉቢቷ ሙዚቃ
ንፁህ እንደ ፀሀይ ዉብ እንደ ጨረቃ

231. ከላይ ለቀረበዉ ግጥም ርዕስ ሊሆን የሚችለዉ የቱ ነዉ ?

ሀ. ሙዚቃ　ለ. ጨረቃ　ሐ. ፀሀይ　መ. ዉቢቷ

232. ሙዚቃ ከጨረቃ ጋር የተነፃፀረችዉ ከሚከተሉት በየትኛዉ ነዉ ?

ሀ. በንፅህና　ለ. በቃና　ሐ. በዉበት　መ. በመዓዛ

233. በግጥሙ ዉስጥ በሣድስ ፊደል የሚጨርሱ ስንት ስንኞች አሉ ?

ሀ. ሁለት　ለ. ስድስት　ሐ. አራት　መ. አምስት

234. ለሦስተኛው ስንኝ መድረሻ ሐረግ የሚሆነዉ የቱ ነዉ ?

ሀ. ከሾፐን ትካዜ　ለ. ከያሬድ ልቦና　ሐ. ከያሬድ　መ. ልቦና

235. ግጥሙ ስንት ስንኞች አሉት ?

ሀ. 4　ለ. 5　ሐ. 12　መ. 6

**መመሪያ አስራ ስምንት፡-** **<u>ከተራ ቁጥር 230 — 239 የቀረቡትን ጥያቄዎች ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ መሰረት ያደረጉ ናቸው:: ምንባቡን በፅሞና በማንበብ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ</u>::**

ገቱኒ! ከበቡኝ። ከመወለዴ ተከበብኩ በብዙ ጥያቄዎች። ከልጅነቴ መጠየቅን ደፈርኩ፤ መጠየቅን ግን ፈራሁ። ጥያቄዎች የራሴ ፣ የውስጤ ይመስሉኝ ነበር። ግን ዙሪያውን ተከብቤያለሁ በጥያቄዎች። ከውጭም እንደከበቡኝ የገባኝ ዘግይቶ ነው። ገብቶኝ ከሆነ ። ብዙ ጊዜ አንድ ነገር የገባኝ መስሎኝ ሳይገባኝ ቀርቷል። እንዲያውም አሁን አሁን የገባኝ እና የመሰለኝ ተቀላቅለው ፣ አንድ ሆነዋል።

ጥያቄዎቹ የከበቡኝ ግን ለምንድ ነው? እንዳልኳችሁ ፣ ጥያቄዎቹ የውስጤ የመሰሉኝስ ለምንድን ነው? ገና ሲጀመር "የውስጤ ማለት ምን ማለት ነው? የ"እኔ" ማለት ይሆን እኔ እና ውስጤ ግን አንድ አይደለንም? ነን? እኔ እንጃ አላውቅም! ውይ …! አላውቅም አልኩ? ሳላስበው።" ልጅ እያለሁ ብዙ አላስብም ነበር። በመሆኑም አላውቅም ማለት አያሳፍረኝም ነበር። አቤት… አቤት አወረድኩት ይኼን መቀባጠር፣ ግን እንዲሁ ነኝ። እጠይቃለሁ፤ ምክንያቱም በጥያቄዎች ተከብቤአለሁ።

በጥያቄ የመከበብ ችግር ምንድን ነው? ምንም መልስ ካለመኖር ውጭ ፣ እውነት ግን መልስ የለም? ያለም የሌለም ይመስለኛል እንደ ፈጣሪ ። ፈጣሪ እና እኔ የቆየ ፣ የጠበቀም የላላም ፣ አንዳንድ ጊዜ የሚዳድር ሌላ ጊዜ የሚሿሿሽ ግንኙነት አለን። ግንኙነታችን የጀመረው በልጅነት ነው። በእኔ ልጅነት ማለቴ ነው። ድንገት ከተምታታባችሁ ፣ አሁን የምታስቡትን እገምታለሁ "ምን አይነት ድፍረት ነው?" ከሚል ጥያቄ ጋር የተያያዘ ሀሳብ በጭንቅላታችሁ ሲጉላላ ይታየኛል። አንዳንድ ሀሳብ ፣ በጭንቅላት ውስጥ ብቻ መጉላላት የተፈረደበት ለምን ይሆን!? እላለሁ። እጠይቃለሁ። ጥያቄ እንዲሁ ከቦኛል። ግን እኔን ብቻ አይደለም ፤ እናንተንም ከቧችኋል። እስኪ ውስጣችሁ ያለውን ሁሉ ጠይቁ በሉ እስኪ "? … መቼም ጉድ ነበር የሚፈላው።

"ወደ ቀድሞ ነገሬ ልመለስ" ይህችን አባባል ከሌላ ቦታ ነው የቃረምኳት። የሚያውቁ ያውቋታል፣ ቢያንስ አባባሏን ከየት እንዳመጧት ፤ የማታውቁ ደግሞ ጠይቁና እወቁ ወይንም ተረዱ። "ወደ ቀድሞው ነገር መመለስ" የሚለውን ግን ማወቅ ምን ይጠቅማል? ይህችን ሃረግ ከየት እንዳመጣኋት ብናገርስ በቃ ጨዋታው ያልቃል ማለት ነው? እኔ ሞጋች ነኝ ፣ ልመዱት። ከእኔ ከሙግት የዘለለ ቁም ነገር እንዳትጠብቁ፡ ፡ ወደ ቀድሞው መመለስ ግን ምን ይጠቅማል። አሁን አብዛኞቻችሁ "የድሮ ናፋቂ" ምን-አምን…" እያላችሁ ማሰብ ካልጀመራችሁ ጥሩ ነው ያላችሁት። አልኩ።

እናንተ ግን ይህን ለምን ታነባላችሁ? ባጠቃላይ ለምን ተነባላችሁ? ምን ፍለጋ እውቀት ፣ እውነት ፣ ወይስ ለምደባችሁ ፣ እኔ ሞጋች ነኝ ብያችኋለሁ። እኔ ማን ነኝ? እስኪ ገምቱ በሞቴ! በናታችሁ….. ገምቱ?

**ምንጭ፡- አለማወቅ ከገፅ *1 - 2***
**ደራሲ፡- ዳዊት ወንድም አገኝ /ዶ/ር/፪፻፲፬**

230. የምንባቡ አንቀፅ አንድ የሚይገልጸው የትኛውን ሃሳብ ነው?

ሀ. በብዙ ጥያቄዎች መከበብ

ሐ. በጥያቄ የመከበብ ችግር ምንድን ነው ለ. የገባኝ መስሎኝ ሳይገባኝ መቅረቱን

መ. ከልጅነቴ መጠየቅን መድፈሬ

231. ከሚከተሉት ውስጥ ለምንባቡ ርዕስ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

ሀ. አለማወቅ ለ. አለማሰብ ሐ. መጠየቅ መ. አለመጠየቅ

232. የምንባቡ አጠቃላይ ሃሳብ ምንድን ነው? ሀ. በጥያቄ የመከበብ ሂደትን ማሳየት

ለ. በማሰብና በመጠየቅ መካከል ያለውን ዝምድና ማሳየት ሐ. ማሰብ መጀመርን ከማወቅ ጋር ማምታታት

መ. የውስጥ ስሜትን ማሳየት

233. በምንባቡ ውስጥ የተገለፀው በጥያቄ የመከበብ ችግር ምንድን ነው? የሚለው ሃሳብ በስንተኛው አንቀፅ ላይ ይገኛል?

ሀ. በአንድ ለ. በሁለት ሐ. በሦስት መ. በአራት

234. ከመወለዴ በብዙ ጥያቄዎች **ተከበብኩ**። በሚለው ዓ.ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ ምንድን ነው?

ሀ. ተወረርኩ ለ. ተያዝኩ ሐ. ከበብኩ መ. በጠላት ጦር መከበብ

235. አንዳንድ ጊዜ **የሚዳድር** ሌላ ጊዜ የሚሟሸሽ ግንኙነት አለን። የተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ፍቹ ምንድን ነው?

ሀ. የሚሟሸሽ ለ. የሚጠነክር ሐ. የሚሟሟ መ. የሚቀንስ

236. ይህችን አባባል ከሌላ ቦታ ነው **የቃረምኩት**። በሚለው ዓ.ነገር ውስጥ ከተሰመረበት ሐረግ ጋር በትርጉም የሚመሳሰለው ከሚከተሉት የትኛው ነው?

ሀ. የበተንኩት ለ. የተዝረከረኩት ሐ. የሰበሰብኩት መ. ያገኘሁት

237. ከልጅነቴ መጠየቅን ደፈርኩ ፤ **መጠየቅን** ፈራሁ። የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ ምንድን ነው? ሀ. መመርመርን ለ. መፈተሽን ሐ. መሞገትን መ. ሁሉም

238. ሃሳብ በጭንቅላት ውስጥ ብቻ **መጉላላት** የተፈረደበት ለምን ይሆን? የተሰመረበት ቃል ተቃራኒ ፍቺ ምንድን ነው?

ሀ. መመላለስ ለ. መውጠንጠን ሐ. መንሰላሰል መ. መቀመጥ

239. ወደ ቀድሞው **መመለስ** ግን ለምን ይጠቅማል? በሚለው ዓ.ነገር ውስጥ ከተሰመረበት ጋር በትርጉም የሚመሳሰለው ከሚከተሉት የትኛው ነው?

ሀ. መውጣት ለ. መዞር ሐ. መጓዝ መ. መሄድ

## መመሪያ አስራ ዘጠኝ፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክለኛውን መልስ ምረጡ።

240. ከበረ ብሎ ክብረት ማለት ከተቻለ ጠለፈ ብሎ______________ ቢባል የቋንቋውን ተናጋሪዎችን ማግባባት ይችላል።

ሀ. ጥልፈት ለ. ጠላፊ ሐ. መጥለፊያ መ. ጥልፍ

241. "ምልሰት" የሚለው የሥነ ፅሑፍ ቃል የያዘው ትርጉም

ሀ. ጨዋታ ለ. የኋላ ታሪክ ሐ. ንግር መ. ትንቢት

242. ከሚከተሉት መካከል ኢ-ልቦለድ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ዘገባ ለ. ማመልከቻ ሐ. ቃለ ጉባኤ መ. ተውኔት

243. ለንግግር ጥንቃቄ ማድረግ ያለብን ፤

ሀ. አድማጭ መልዕክቱን በአግባቡ መረዳት ስላለበት ነው። ለ. ያለመግባባትን ለመቀነስ ሲባል ነው።

ሐ. አድማጭ ንግግራችን ሲያዳምጥ እንዳይሰለቻቸው ስለሚፈልግ ነው መ. ሁሉም መልስ ነው።

244. ልዩ የሆነው የቱ ነው

ሀ. ትልም ለ. ግጭት ሐ. ታሪክ መ. ሐተታ

245. ከሚከተሉት አንዱ ስማዊ ሀረግ ነው፤

ሀ. የአዋሽ ወይን ጠጅ ሐ. ወይን ጠጅ ተሸጠ

ለ. የወይን ጠጁ ጣፋጩ መ. እንደ ወይን ጠጅ ጣፈጠ

246. ከአጭር ልቦለድ አላባዊያን መካከል የልቦለድ ታሪክ የተፈጸመበትን ጊዜና ቦታ የሚያመለክተው አላባ የቱ ነው?

ሀ. ግጭት ለ. መቼት ሐ. ሴራ መ. ጭብጥ

247. በልቦለድ ውስጥ የምክንያና የውጤት ትስስር ______________________ ይባላል።

ሀ. መቼት ለ. አንጻር ሐ. ሴራ መ. ግጭት

248. ከሚከተሉት መካከል በእውነት ላይ ያልተመሰረተው የቱ ነው?

ሀ. ማስታወቂያ ለ. ልቦለድ ሐ. የህይወት ታሪክ መ. ደብዳቤ

249. የሚያስጠጋው ነጻ ምዕላድ የመጨረሻ ፊደል ሳድስ ሲሆን የምንጠቀመው አብዥ ቅጥያ ምዕላድ__ነው?

ሀ. "-ኣት" ለ. "-ኣን" ሐ. "-ኦች" መ. "-ዎች"

250. አንድ ድርሰት ለመጻፍ እንደ አቅጣጫ ጠቋሚ የምንጠቁምበት መሳሪያ ______________ ይባላል? ሀ. ርዕስ ለ. ቢጋር ሐ. ድርሰት መ. ሐተታ

251. ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚካሄድ ኢ-መደበኛ ውይይት ____________ ይባላል? ሀ. ጭውውት ለ. ክርክር ሐ. ውይይት መ. ቃለመጠየቅ

252. ከሚከተሉት መካከል የክርክር ዝግጅት መመሪያ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ልምምድ ማድረግ ሐ. ሁሉንም ነገር አለማንበብ

ለ. ርዕስን ማስተዋወቅ መ. ምስጋና ማቅረብ

253. መዲና በጣም ከፉኛ ታማለች። በዚህ ዓ.ነገር ተውሳከ ግሳዊ ሀረጉ የቱ ነው?

ሀ. ክፉኛ ለ. በጣም ክፉኛ ሐ. ክፉኛ ታማለች መ. ልጁ በጣም

254. "ንግር" የሚለው የሥነ-ፅሑፍ ቃል የያዘው ትርጉም

ሀ. ጨዋታ ለ. የኂላ ታሪክ ሐ. ምልሰት መ. ትንቢት

255. **<u>ጥራዝ ነጠቅ</u>** እውቀት ግልብ ያደርጋል። የተሰመረበት ፈሊጣዊ አነጋገር ፍቺ ከሚከተሉት የትኛው ነው?

ሀ. ግልብ እውቀት ያለው ሐ. ጥልቅ ትምህርት የሌለው

ለ. ብዙ ያልተማረ መ. ሁሉም

256. ልጂቷ **<u>አይነ ልም</u>** ናት። የተሰመረበት ፈሊጣዊ አነጋገር ፍቺ ከሚከተሉት የትኛው ነው?

ሀ. ቆንጆ ለ. ምቀኛ ሐ. ተንኮለኛ መ. የዋህ

257. በአንድ አውራ ጎዳና ላይ ብዙ መኪናዎች ተጋጩ____________________ በህይወት ላይ የደረሰው ጉዳት ትንሽ ነበር። ባዶ ቦታውን የሚያሟላው አያያዥ የቱ ነው?

ሀ. እንዲያውም ለ. ሆኖም ሐ. በዚህም የተነሳ መ. በመሆኑም

258. ከሚከተሉት ቃላት ኢ- ተዘውታሪ ቃል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ህዳግ ለ. ሙዳ ሐ. ህፀፅ መ. መስመር

259. አስተዋዩ ተማሪ ውድድሩን አሸነፈ። በሚለው ዓ.ነገር ግሳዊ ሀረጉ የቱ ነው?

ሀ. አስተዋይ ተማሪ ለ. አስተዋይ ሐ. ውድድሩን አሸነፈ መ. ውድድሩን

260. ዘይነባ አክስቷን ለመጠየቅ ወደ ድሬደዋ ሄደች። በሚለው ዓ.ነገር ውስጥ መስተዋድዳዊ ሀረጉ የቱ ነው?

ሀ. አክስቷን ለ. ወደ ድሬደዋ ሐ. አክስቷን በመጠየቅ መ. ሄደች

261.ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ልዩ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ደለበ ለ. ወፈረ ሐ. መነመነ መ. ፈረጠም

262. ቅድስት እናቷ ስለታመሙ አዘነች። በሚለው ዓ.ነገር ውስጥ በመንስኤነት የተጠቀሰው የትኛው ነው?

ሀ. ማዘኗ ለ. ቅድስት ሐ. እናቷ መ. የእናቷ መታመም

263. ልጅ ካሳ ከእናታቸው ከእመት አትጠገብ ወንድወሰንና ከአባታቸው ከጌታቸው ሀይሉ በ1811 ዓ.ም በቋራ ተወለዱ። ይህ ፅሁፍ ለየትኛው የድርሰት አይነት ምሳሌ ሊሆን ይችላል።

ሀ. ገላጭ ለ. ስዕላዊ ሐ. ተራኪ መ. አከራካሪ

264. ከሚከተሉት ጥንድ ቃላት በፍካሪያዊ የገባው የቱ ነው?

ሀ. መሰላል/መወጣጫ ለ. በግ/እንስሳ ሐ. ሲባጎ/ገመድ መ. ባህር/ሠፊ

265. **ንብ** የሚለው ቃል እማሬያዊ ትርጉም የቱ ነው?

ሀ. ታታሪ ለ. ትጉህ ሐ. በራሪ ፍጡር መ. ሰራተኛ

266. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ገቢር ግስ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ሰበረ ለ. ለወጠ ሐ. ቀደደ መ. ተጠበሰ

267. ቤት ለመስራት በመጀመሪያ ሀምሳ ሴንቲ ሜትር ስፋት ወደታች ንጣፍ ድንጋይ እስከሚገኝ ድረስ ይቆፈራል። ይህ ፅሁፍ ለየትኛው የድርሰት አይነት ምሳሌ ሊሆን ይችላል?

ሀ. ስዕላዊ ለ. አስረጂ ሐ. ተራኪ መ. አመዛዛኝ

268. እሰይ! ልጄ በጥሩ ውጤት ተመረቀችልኝ። የሚለው ዓ.ነገር ከዓ.ነገር አይነቶች ከየትኛው ይመደባል?

ሀ. አጋናኝ ለ. ትዕዛዛዊ ሐ. ጥያቄያዊ መ. ሐተታዊ

269. ልጁ **እጅግ በጣም ጎበዝ** ነው። በሚለው ዓ.ነገር የተሰመረበት ምን አይነት ሀረግ ነው? ሀ. ቅፅላዊ ሀረግ

ሐ. መስተዋድዳዊ ሐረግ

ለ. ስማዊ ሀረግ መ. ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ

270. የቤት ሥራችሁን በአግባቡ ስርታችሁ ኑ! የሚለው ዓ.ነገር ከዓ.ነገር አይነቶች ከየትኛው ይመደባል?

ሀ. አውንታዊ ለ. አሉታዊ ሐ. መጠይቃዊ መ. ትዕዛዛዊ

271. "በግ" ለሚለው ቃል እማሬያዊ ፍቹ፧

ሀ. የዋህ ለ. ታርዶ የሚበላ እንስሳ ሐ. ገራም መ. ገር

272. ከሚከተሉት ቃላት አንዱ ቅድመ ግንድ ቅጥያ አለው።

ሀ. አሰተኛ ለ. ሰዎች ሐ. ትላልቅ መ. ሠራተኞች

273. አንድ የልቦለድ መፅሐፍ አንባቢ ፤ "ከዚህ ቀጥሎ ምን ይፈጸም ይሆን? ምን ውጤት ይከተላል እያለ ቢጠይቅ ስለ________________መጨነቁ ነው።

ሀ. መቼት ለ. የቋንቋ አጠቃቀም ሐ. ታሪክ መ. የትረካ አንጻር

274. ለምን ሁልጊዜ ትረብሻለህ? የሚለው ዓ.ነገር ከዓ.ነገር አይነቶች ከየትኛው ይመደባል?

ሀ. ትዕዛዛዊ ለ. ጥያቄያዊ ሐ. አጋናኝ መ. ሐተታዊ

275. ልጁ ትናንትና መፅሐፍ አልገዛም። የሚለው ዓ.ነገር ከዓ.ነገር አይነቶች ከየትኛው ይመደባል? ሀ. አሉታዊ ለ. አውንታዊ ሐ. ጥያቄያዊ መ. ትዕዛዛዊ

276. ከሚከተሉት በአማራጭነት ከቀረቡት ርዕሶች አንዱ አመዛዛኝ (አወዳዳሪ) ድርሰት ለመጻፍ ያስችላል።

ሀ. የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሐ. የማልረሳው ቀን ትዝታ

ለ. ምናብ እና እውቀት **መ. የጦር ሜዳ ውሎ ታሪክ**

277. የሰንጎ መገን ቤት የሚባለው የግጥም አይነት________________________ቀለማት አሉት።

ሀ. አስር ለ. ስምንት ሐ. አስራ ሁለት መ. አስራ ስድስት

278. "ደግሞ እኮ አላፍር ብሎ በማግስቱ ተመልሶ መጣ።" አባባሉ ምን ይገልጻል?

ሀ. አድናቆት ለ. ግርምትን ሐ. እልህን መ. አክብሮትን

279. ቢቆጣት አትሰማ ፣ ቢመክራት አትመች፤ ፊቷን አላይ ብላ አመድ መስላ ዋለች። ከላይ የቀረበው ቅኔ ወርቁ ምንድን ነው?

ሀ. ፊቷን በመስታውት አላይ ብላ ሐ. ከፊት ለፊት የሚጠብቃትን አላስተውል ብላ ለ. ፊቷን አላይ ብላ መ. ፊቷን በመስታውት አይታ

280. አንድን መረጃ ከውስጥ ወደ ውጭ የምናስተላልፍበት ክሂል ምንድን ነው?

ሀ. በማንበብ ለ. በመጻፍ ሐ. በመናገር መ. ለ እና ሐ

281. እናቴ ከባህርዳር <u>**አገልግል**</u> ላከችልኝ። የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ ምንድን ነው?

ሀ. እርዳ ለ. አግዝ ሐ. ምግብ መያዣ መ. ስጥ

282. የማንኛውም ቋንቋ መዋቅር መሰረቱ________________________ነው?

ሀ. ቃል ለ. ድምፅ ሐ. ፊደል መ. ምዕላድ

283. ወይ የኔ ጌታ ዋርካ ነህ ዋርካ፤ ቢጠለሉብህ የማታስነካ። ከላይ የቀረበው ሥነ ቃል ወይም ግጥም ከየትኛው ይመደባል?

ሀ. የሙገሳ ለ. ሙሾ ሐ. የሰርግ መ. የፉከራ

284. ____________ አእምሯችን እንዲቀላጠፍና ፣ ጥልቅ የሆነ የማሰብ ችሎታ እንዲኖረንና ነገሮችን በቀላሉ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር የሚረዳ ጥበብ ነው፡፡

ሀ. ፈሊጣዊ አነጋገር ለ. ቅኔ ሐ. ምሳሌያዊ አነገጋር መ. ዘይቤ

285. የሚያስጠጋው ነጻ ምዕላድ የመጨረሻ ፊደል ከሳድስ ውጭ ሲሆን የምንጠቀመው አብዥ ቅጥያ ምእላድ_ ነው?

ሀ. "-ኦች" ለ. "-ዎች" ሐ. "-ኣት" መ. "-ኣን"

## መመሪያ ሀያ፡- ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ትርጉማቸውን ምረጡ::

286. ሐሞቱ ፈሰሰ

ሀ. ተሸነፈ ለ. በረታ ሐ. ወኔው ተሰለበ መ. ጀግንነት አሳየ

287. ሲበሉ የላኩት

ሀ. ንቁ ለ. ልበቢስ ሐ. መቅኖ ቢስ መ. ፈጣን

288. ሆደ ባሻ

ሀ. ቶሎ የሚከፋው ሐ. በቀላሉ ስሜቱ የሚጎዳ

ለ. አኩራፊ መ. መልሱ አልተሰጠም

289. "አድራጊ ፈጣሪ" ሲል________________________ ማለቱ ነው?

ሀ. ፈላጭ ቆራጭ ሐ. ሁሉን ማድረግ የሚችል

ለ. ሥልጣን ያለው መ. ሁሉም መልስ ነው

## መመሪያ ሀያ አንድ፡- ከተራ ቁጥር 290 — 299 የቀረቡትን ጥያቄዎች ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ መሰረት ያደረጉ ናቸው:: ምንባቡን በፅሞና በማንበብ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ::

### ጀምሮ የመጨረስ ምስክርነት

በሀገሩ በከፊል በግብርና ሥራ ይተዳደር የነበረው ጆን (John Stepphen Akhwari) በፈረንጆች አቆጣጠር በ1968 ዓ.ም በሜክሲኮ ከተማ ውስጥ በተደረገው የማራቶን ውድድር ለመሳተፍ በሄደበት ጊዜ በውድድሩ መካከል ላይ በደረሰበት ችግር ምክንያት በመውደቁ ጉልበቱና ትከሻውን ላይ ጉዳት ይደርስበታል፡፡ ቢዚህ ጉዳት ውስጥ ሆኖ እንኳን የጀመረውን ሳይጨርስ ላለማቆም የነበረውን ቁርጠኝነት እስከአሁን ድረስ በዓለም ዙሪያ በምሳሌነት ይነገርለታል፡፡

በታዋቂው ኢትዮጵያዊ ሯጭ በማሞ ወልዴ አሸናፊነት በተጠናቀቀው በዚህ የማራቶን ውድድር ወቅት በወቅቱ የ26 ዓመት እድሜ የነበረው ጆን በደረሰበት ጉዳት ምክንያት በድንገት ቢወድቅም ከወደቀበት ተነስቶ

እያነከሰ ውድድሩን ለማጠናቀቅ በቃ ይህ ሁኔታ ከተከሰተ ከ52 ዓመታት በኋላ በተደረገለት ቃለ መጠይቅ ላይ ልምምዱን በማስታወስ ሲገልፅ፣ "የ42 ኪሎ ሜትሩን ሩጫ ጀምሬ 30 ኪሎ ሜትር እንደሮጥኩኝ ነበር እጅግ በጣም የህመም ስሜት የተሰማኝ፡፡ እኔ ግን ውድድሩን ማቆም የሚባለውን ነገር በፍጹም አላሰብኩም" ይላል በደረሰበት ድንገተኛ ህመም ወድቆ የነበረው ጆን፣ በዚህ ጉዳትና ስቃይ ውስጥ ሆኖ ነበር ከወደቀበት ተነስቶ እያነከሰ፣ ምንም እንኳን መጨረሻ ቢወጣም ውድድሩን የጨረሰው፡፡

ይህ አንደኛ ስለወጣ ሳይሆን የጀመረውን ሳይጨርስ ባለማቆሙ ምክንያት በዓለም ዙሪያ እስከ አሁን ብዙዎችን በማነሳሳት የሚታወቀው ሰው በየጊዜው የሚጠቀስለትን ታዋቂው ንግግሩ እንዲህ የሚል ነው፡፡ ሃገሬ የላከኝ የሩጫ ውድድሩን እንድጀምር ሳይሆን እንድጨርስ ነው፡፡

ጆን "መጨረሻ የወጣው አሸናፊ" በመባል ይታወቃል፡፡ ምንም እንኳን ሩጫውን በተዘጋጀበትና በፈለገበት መልኩ ባያሸንፍም በነበረው ጀምሮ የመጨረስ ቁርጠኝነት አንጻር ግን ጨርሶታል፡፡ በወቅቱ ከቁጥጥር ውጭ ከነበረው ሁኔታ በላይ በመነሳት ሩጫውን ጨርሷል፡፡ ሩጫውን አላቋረጠም ፣ ሩጫውንም የጨረሰው ደግሞ በሃፍረት አንገቱን በመድፋት አልነበረም፡፡ በወቅቱ የነበረውን አቅም በሙሉ በመጠቀም ጥጉ ድረስ በመሮጡ በኩራት ቀና ብሎ ነው፡፡

ጆን ያንን ሩጫ እስከ ጥጉ ከሮጠ በኋላ መጨረሻ ሆኖ በማጠናቀቁ ምንም አይነት የደረጃ ሽልማት ባያገኝም ከዚያ በኋላ ግን የበርካታ ሽልማቶች ባለቤት ሆኗል በዓለም ዝነኛና ለብዙ ሰዎች ጀምሮ የመጨረስን ምስጢር ያስተዋወቀ ሰው ሆኖ ይነገርለታል፡፡ በዓለም ዙሪያ ይህንን መሰል ተቀባይነት ያገኘው የጀመረውን ሩጫ ሳይጨርስ ለማቆም አሻፈረኝ በማለቱ ነው፡፡

***ምንጭ፡- (ጀምሮ መጨረስ ከሚለው ከዶ/ር ኢዩብ ማሞ መፅሐፍ ከገፅ 17-18) (2021 እ.ኤ.አ)***

290. **<u>እያነከሰ</u>** ዉድድሩን ለማጠናቀቅ በቃ፡፡ የተሠመረበት ቃል አዉዳዊ ፍቺ ምንድን ነዉ? ሀ. ተወጫመደ

ሐ. ጎንበስ ቀና አለ

ለ. ጠንቀስ ጠንቀስ አለ

መ. ሁሉም

291. ጆን _____________________ በመባል ይታወቃል?

ሀ. የተሸነፈዉ አሸናፊ

ሐ. መጨረሻዉ የወጣዉ አሸናፊ

ለ. መጀመሪያ የወጣዉ አሸናፊ

መ. ያሸናፊዉ ተሸናፊ

292. ተቀባይነት ያገኘዉ የጀመረዉን ሩጫ ሳይጨርስ ለማቆም **<u>አሻፈረኝ</u>** ማለቱ ነው፡፡ የተሰመረበት ቃል አዉዳዊ ፍቺ ምንድን ነዉ፡፡

ሀ. አልታዘዝም ለ. አልሰራም ሐ. አልከውንም መ. እምቢ

293. "ሀገሬ የላከኝ የሩጫ ዉድድሩ እንድጀምር ሳይሆን እንድጨረስ ነዉ።" የሚለዉ ሀሳብ ስንተኛዉ አንቀፅ ላይ ይገኛል?

ሀ. አንደኛዉ ለ. ሁለተኛዉ ሐ. ሦስተኛዉ መ. አራተኛዉ

294. የዚህ ማራቶን ዉድድር በማን አሸናፊነት ተጠናቀቀ

ሀ. በጆን ስቴፈን ለ. በማሞ ወልዴ ሐ. በአበበ ብቂላ መ. በሀይሌ ገ/ስላሴ

295. ሩጫዉ የተካሄደዉ በፈረንጆች አቆጣጠር____________________ ዓ.ም ነዉ።

ሀ. 1968 ለ. 1960 ሐ. 1976መ. 1970

296. ዉድድሩ የተካሄደዉ የት ሀገር ነበር?

ሀ. ጀርመን ለ. ፈረንሳይ ሐ. ሜክሲኮመ. ሩሲያ

297. ይህ ሁኔታ ከተከሰተ ከስንት ዓመት በኂላ ቃለ መጠየቅ ተደረገለት?

ሀ. 52 ለ. 42 ሐ. 32መ. 22

298. ጆን የሩጫ ዉድድሩን ስንተኛ ሆኖ አጠናቀቀ?

ሀ. አንደኛ ለ. ሦስተኛ ሐ. ሁለተኛመ. መጨረሻ

299. ጆን ስንት ኪሎ ሜትር እንደሮጠ እጅግ በጣም ህመም ተሰማዉ?

ሀ. 30 ለ. 25 ሐ. 35መ. 20

## መመሪያ ሀያ ሁለት፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ልዩ ልዩ ጥያቄዎች እንደ አጠያየቃቸው ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

300. ቤት ሲሰራ ዋናው ብረቱ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው መሰረት ነው። ያልጠነከረ ቤት እድሜ አይኖረውም። ቤት የሚሰራ ሰው ሁሉ ለመሰረቱ ጥንካሬ ቅድሚያ መስጠት አለበት። ይህ ፅሁፍ ለየትኛው የድርሰት አይነት ምሳሌ ሊሆን ይችላል?

ሀ. ተራኪ ለ. አመዛዛኝ ሐ. ስዕላዊ መ. አስረጂ

301. ውይይት ሲጀመር ተወያዮች ጉዳዩን አስቀድመው እንዲያስቡበት አወያዩ በቅድሚያ የሚያደርገው ነገር ምንድን ነው?

ሀ. የውይይቱን ተሳታፊዎች መለየት ሐ. የውይይትን አጀንዳ ማስተዋወቅ

ለ. የውይይቱን ውሳኔ ግልፅ ማድረግ መ. ውይይቱን በሥነ-ሥርዓት መምራት

302. በአንድ ፅሁፍ ውስጥ ቦታና ጊዜ የተገኙና ያልተገኙ አባላት ስምና አጀንዳ ተፅፎ ከተገኘ ያንን ፅሁፍ ምን ብሎ መጥራት ይቻላል?

ሀ. ዘገባ ለ. ደብዳቤ ሐ. ቃለ ጉባኤ መ. ማስታወቂያ

303. ከቋንቋ ክሂሎች ቀዳማይ የሆነው ዘርፍ የትኛው ነው?

ሀ. መናገር ለ. መጻፍ ሐ. ማንበብ መ. ማዳመጥ

304. አየለች የትምህርት **<u>ፍላጎቷ</u>** ዝቅተኛ ነው። ለተሰመረበት ቃል ፍቺ የሚሆነው የቱ ነው? ሀ. ጭንቀቷ ለ. እቅዷ ሐ. ጥረቷ መ. ዝንባሌዋ

305. የጠቡ **<u>ሰበብ</u>** ምንድን ነው። ለተሰመረበት ቃል ፍቺ የሚሆነው የቱ ነው?

ሀ. መዘዝ ለ. ሳንካ ሐ. ውጤት መ. ችግር

306. አንድ ተማሪ ለመምህሩ **<u>ተገቢውን</u>** አክብሮት መንፈግ የለበትም ለተሰመረበት ቃል ፍቺ የሚሆነው የቱ ነው?

ሀ. የሚቸረውን ለ. የሚጠብቀውን ሐ. አስፈላጊውን መ. የሚሰጠውን

307. "መጥፎ ንግግሩ አንጀቴን **<u>ቆረጠው</u>**።" ለተሰመረበት ቃል ተስማሚ ፍቺ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?

ሀ. አሳቀቀኝ ለ. አስቀየመኝ ሐ. አታለለኝ መ. አስለቀሰኝ

308. የሁላችንንም **<u>ቀልብ የሳበ</u>** ነገር ተከሰተ። ለተሰመረበት ሐረግ ተመሳሳይ ሊሆን የሚችለው ቃል የትኛው ነው?

ሀ. የጎተተ ለ. ያስለቸ ሐ. የማረከ መ. ያተኮረ

309.ከሚከተሉት መካከል ልዩ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ኩራዝ ለ. ጉቶ ሐ. ገንቦ መ. አውራ

**መመሪያ ሀያ ሶስት፡- <u>ከጥያቄ ቁጥር 310-314 የቀረቡት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረቡት ዓ.ነገሮች ላይ የተመሰረቱ ናቸው:: በመሆኑም ከየትኛው የዓ.ነገር አይነት እንደሚመደቡ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምረጡ</u>::**

310.ጎበዝ ተማሪ በርትቶ ያጠናል።

ሀ. ሐተታዊ ለ. ትዕዛዛዊ ሐ. አጋናኝ መ. ጥያቄያዊ

311.የቤት ሥራህን ሥራ!

ሀ. ጥያቄያዊ ለ. አጋናኝ ሐ. ሀተታዊ መ. ትዕዛዛዊ

312.ለምን ሁል ጊዜ ትረብሻለህ?

ሀ. አጋናኝ ለ. ሐተታዉ ሐ. ጥያቄያዊ መ. ትእዛዛዊ

313. ልጁ ትናንትና ደብተር አልገዛም።

ሀ. ትዕዛዛዊ ለ. ሐተታዊ ሐ. አጋናኝ መ. ጥያቄያዊ

314. እሰይ! ልጄ በጥሩ ውጤት ተመረቀችልኝ።

ሀ. አጋናኝ ለ. ትዕዛዛዊ ሐ. ጥያቄያዊ መ. ሐተታዊ

**መመሪያ ሀያ አራት፡- <u>ከጥያቄ ቁጥር 315 -319 ለቀረቡት ቃላት ልዩ የሆነውን ከተሰጡት አማራጮች መካከል በመምረጥ መልሱ</u>::**

315.ሀ. ባዝራ ለ. ቁብ ሐ. ጊደር መ. ኮረዳ

316.ሀ. ጤፍ ለ. ዘንጋዳ ሐ. ማሽላ መ. በቆሎ

317.ሀ. ሞፈር ለ. ቀንበር ሐ. ድግር መ. መንሽ

318.ሀ. ጀበና ለ. ድስት ሐ. ቅል መ. እንስራ

319.ሀ. ክራር ለ. ዋሽንት ሐ. በገና መ. ማሲንቆ

**መመሪያ ሀያ አምስት፡- <u>ከጥያቄ ቁጥር 320-324 ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቺያቸውን ከተሰጡት አማራጮች መካከል በመምረጥ መልሱ</u>::**

320.ጉዳት ሀ. ህመም ለ. መከፋት ሐ. ጥቅም መ. ችግር

321.የግል ሀ. የጋራ ለ. የሰው ሐ. የአንድ መ. የነጠላ

322.ህቡዕ ሀ. ድብቅ ለ. ስውር ሐ. ሚስጥራዊ መ. ግልፅ

323.ሁከት ሀ. ሰላም ለ. ብጥብጥ ሐ. ነውጥ መ. ሽብር

324.ኢምንት ሀ. ቅንጣት ለ. ትንሽ ሐ. ጥቂት መ. ብዙ

**መመሪያ ሀያ ስድስት፡- <u>ከጥያቄ ቁጥር 325-329 ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ተመሳሳይ ፍቺያቸውን የሚሆነውን ምረጡ</u>::**

325. የቀለም ቀንድ

ሀ. የቀለም መበጥበጫ ሐ. ቀንድ መቀቢያ

ለ. የቀለም ማስቀመጫ መ. አዋቂ

326.የልጅ አዋቂ

ሀ. ልበቢስ ለ. ዝንጉ ሐ. አስተዋይ መ. ቀልበ ቢስ

327. የወሬ ወሬ

ሀ. ጭምጭምታ ለ. ሹክሹክታ ሐ. የተረጋገጠ ወሬ መ. በአደባባይ የተነገረ

328. ጆሮ ስጠኝ

ሀ. አውሰኝ ለ. አዳምጠኝ ሐ. የተረጋገጠ ወሬ መ. ተረዳኝ

329.ቀንበር ሰበረ

ሀ. ህግ አከበረ ለ. ሰነጠቀ ሐ. አነከተ መ. ህግ ተላለፈ

**መመሪያ ሀያ ሰባት፡- ከጥያቄ ቁጥር 330-335 በሚከተሉት ዓ.ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ፍቺ የሚሆኑትን ምረጡ::**

330. ሀውለት ገና **በለጋነቷ** የቤቱን ሥራ ተሸከመች።

ሀ. በወጣትነቷ ለ. በእምቦቀቅላነቷ ሐ. በጮርቃነቷ መ. በህጻንነቷ

331. ልጅን ዘመድ ጋር **ልኮ** ማስተማር የተለመደ ነው።

ሀ. ሰዶ ለ. አስተላልፎ ሐ. አስገብቶ መ. አምጥቶ

332. በርካታ የአስናቀች **እኩዮች** ከተማን እንዲናፍቁ አስገድዷቸዋል።

ሀ. ባልደረቦች ለ. ቤተሰቦች ሐ. ዘመዶች መ. መሰሎች

333. ፊቷ **የመወየብ** ምልክት ቢታይበትም ጠይምና መልከ መልካም ናት።

ሀ. የመዋብ ለ. የመቅላት ሐ. የመክሳት መ. የመገርጣት

334. የሁለቱ ዓ.ነገሮች ቁርኝት **ልል** ነው።

ሀ. ጥብቅ ለ. ጥብቅ ያልሆነ ሐ. የተያያዘ መ. የተቆራኘ

335. የኤልሳቤጥ አባት **ለጋስ** ናቸው።

ሀ. ንፉግ ለ. ሰጪ ሐ. ስስታም መ. ቅቅታም

**መመሪያ ሀያ ስምንት፡- ከተራ ቁጥር 336— 339 ለሚከተሉት ቃላት ፍካሬያዊ ፍቺያቸው የሚሆነውን ምረጡ::**

336. እሳት ሀ. የሚነድ ለ. ነበልባል ሐ. ፈጣን መ. የሚቀጣጠል

337. ነብር ሀ. ጠጉረ ዥንጉርጉር ለ. የዱር አራዊት ሐ. የዱር እንሰሳት መ. ሀይለኛ

338.ጎጆ ሀ. ትዳር ለ. ትንሽ ቤት ሐ. መኖሪያ መ. የሳር ቤት

339. እናት ሀ. እርግዛ የወለደች ለ. ሩህሩህ ሐ. አሳዳጊ መ. ሴት ሞግዚት

**መመሪያ ሀያ ዘጠኝ፡- ከተራ ቁጥር 340 —— 344 ለሚከተሉት ቃላት ቀጥተኛ ፍቺ የሚሆነውን ምረጡ::**

340. መባቻ ሀ. አጥቢያ ለ. ንጋት ሐ. ተከታይ መ. መጀመሪያ

341. ማግስት ሀ. መጀመሪያ ሐ. የማንኛውም ቀን ተከታይ ለ. የወር መግቢያ መ. የወሩ መጀመሪያ

342. ረባዳ ሀ. ዘባጣ ለ. ተራራ ሐ. ሜዳ መ. ከፍተኛ ስፍራ

343. ተበተበ ሀ. ጠመጠመ ለ. ጎነጎነ ሐ. አሰረ መ. ሁሉም

344. ምድረ በዳ ሀ. ልምላሜ ለ. አረንጓዴ ሐ. በእፅዋት የተሸፈነ መ. በረሃ

**መመሪያ ሰላሳ፡- ከተራ ቁጥር 345-349 በሚከተሉት ዓ.ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ተቃራኒ ፍቺ የሚሆኑትን ምረጡ፡፡**

345. የክፍላችን አለቃ ፀባዬ **ሠናይ** ነው።

ሀ. መጥፎ ለ. መልካም ሐ. መሰሪ መ. ተንኮለኛ

346. ጎጂ ድርጊቶች የአንድ ነገር እድገት **ይጎትታሉ**።

ሀ. ያፋጥናሉ ለ. ያዘገያሉ ሐ. ያንትታሉ መ. ያንቀራፍፋሉ

347. የመይሙና አባት **ንፉግ** ናቸው፡፡

ሀ. ስስታም ለ. ሰሱ ሐ. ለጋስ መ. ቅቅታም

348. በዝናብ ብዛት የተነሳ መሬቱ **ወረዛ**።

ሀ. ረጠበ ለ. ደረቀ ሐ. አዝ መ. ራሰ

349. የመንደሩ ነዋሪዎች የመስኖ **ተጠቃሚ** ናቸው፡፡

ሀ. ተገልጋይ ለ. ትርፍ የሚገኙ ሐ. ረብ መ. ተጎጂ

## ምንባብ

"የለውጥ ኃይል ከሆነው ወጣት ጋር አለም በኤድስ ላይ ይነሳ" የኤድስ መስፋፋት በአለማችን ላይም ሆነ በሀገራችን ላይ እያደረሰ ካለው ጉዳት የተደረገው የማሳወቅና የመከላከል እንቅስቃሴ አነስተኛና ያልተቀናጀ ነበር፤አሁን ግን እየታየ ያለው ጅማሮ ተስፋ ሰጪ ነው። የኤድስ ደዌ በሀገራችን ላይ ከተከሰተ ወዲህ ወረርሽኙ ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ እየተዛመተ መጥቷል፡፡ በአለማችን በበሽታው ከተጠቁት ህሙማን ከ47 ሚሊዮን በላይ ሲሆኑ ከእነዚህም መካከል 14 ሚሊዮኑ አርፈዋል፡፡ የሀገራችንን ሁኔታ ስንመረምር ኤድስን በተመለከተ በአጭር ጊዜ ውስጥ የህሙማኑና የቫይረሱ ተሸካሚዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚያስደነግጥ ቁጥር እየጨመረ መጥቷል፡፡ በዚሁ መሰረት እስከ መስከረም 30/1991 ድረስ 69.931 የኤድስ ህሙማን መኖራቸውን ከተለያዩ ዘገባዎች ማወቅ ተችሏል፡፡ በተደረገው ጥናት መሰረት በሀገራችን ለአቅመ አዳም እና ሔዋን ከደረሱ 7.4 በመቶ የሚሆኑ የቫይረሱ ተሸካሚ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ኤድስ በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብ ላይ ከፍተኛ ማህበራዊ ፣ምጣኔ ሀብታዊና ስነ-ልቦናዊ ተፅእኖ አሳድሯል፡፡ በሽታው በግለሰቦች ላይ ያደረሰው ስቃይና ሞት በተጨማሪ ቤተሰብ ላይ የሚያስከትላቸው ችግሮች <u>እጥፍ ድርብ</u> ናቸው፡፡ ኤድስ በይበልጥ የሚያጠቃው በአፍላ የእድሜ ዘመን ውስጥ ያሉ ጎልማሶችንና አምራች ኃይሎችን በመሆኑ በሀገራችን የተያዘው የልማት እንቅስቃሴ ላይ የሚያስከትለው ችግር ቀላል አይደለም ፡፡

በሀገራችን ኤድስ እንደሰደድ እሳት መዛመት በአብይ ምክንያትነት የሚጠቀሰው የማህበረሰቡ አመለካከት የባህሪ ለውጥ ሊያመጣ አለመቻል ነው፡፡ ለዚህ ባህላዊ ኃይማኖታዊና ምጣኔያዊ ተጽእኖዎች ከፍተኛ አስተዋጽዎ እያረጉ መሆኑ ይታመናል፡፡ በርካታ ወገኖቻችን በኤድስ ሲረግፉ በአይናችን እያየን የባሕሪ ለውጥ አለማሳየትና በሽታው የለም ብሎ መዘናጋት ሞኝነት ወይም ራስን ማታለል ነው፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ የሚጠበቀው የባህሪ ለውጥ የተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን ግንባር ቀደም ሚና አላቸው በተጨማሪም ወላጆች የሙያ ማህበራት ወዘተ ተወናጅተው ተከታታይነት ያለው ቅስቀሳና ትምህርት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ እስከዛሬ መድኃኒት ያልተገኘለት ጨፍጫፊ ደዌ መግታት የሁሉም ያላሰለሰ ጥረት ያሻልና ላፍታ እንኳን ልንዘናጋ አይገባም፡፡

አዲስ ዘመን ጥር 5 ቀን 1991

## መመሪያ ሰላሳ አንድ፡- በምንባቡ መሰረት ከተራ ቁጥር 350- 365 ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

350. በሽታ ለሚለው ቃል ከምንባቡ ውስጥ የሚመሳሰለው አቻ ፍቺ ____________ነው;

ሀ. ቁምሳጥን ለ.ደዌ ሐ. ወረርሽን መ. ተስቦ

351. ወንዱንወጣት ለአቅመ አዳም ደረሰ ስንል ሴቷን ኮረዳ ደግሞ__________________ደረሰች እንላለን;

ሀ. ለሙሽራ ለ. ለአቅመ ትዳር ሐ. ለአቅመ ሄዋን መ. ለአቅመ ጋብቻ

352. "በላቀ ሁኔታ እየተዛመተ መጥቷል" ሲል__________________ማለቱ ነው;

ሀ. በረቀቀ ዘዴ እየተስፋፋ ነው ሐ. ባልታወቀ መንገድ እየተዛመተ ነው ለ. በብዙ ስፍራዎች እየተበራከተ ነው መ. በከፍተኛ መጠን እየተሰራጨ ነው

353. ኤድስ እንደሰደድ እሳት መዛመት ሲል፡ -____________

ሀ. ኤድስ ሰዎችን እያቃጠለ በማሰቃየት ላይ መሆኑን ያመለክታል

ለ. ኤድስ ፋታ የማይሰጥ ሰዎችን በመግደል ላይ መሆኑን ያንፀባርቃል

ሐ. ለመግታት ባልተቻለ መንገድ የኤድስ በሽታ በመሰራጨት ላይ መሆኑን ያንፀባርቃል መ. ኤድስ በሀገራችን ውስጥ ቀስበቀስ በመሰራጨት ላይ መሆኑን ያሳያል

354. "ሞኝነት ወይም ራስን ማታለል ነው" የሚለው ____________________ለማንፀባረቅ ነው;

ሀ. ኤድስን ለመከላከል ጥንቃቄ አለማድረግ ሐ. ቅስቀሳና ትምህርት አለመስፋፋቱ ለ. ጨፍጫፊ የሆነ ደዌ ለመታደግ አለመቻል መ. የኤድስ ወረርሽኝ ቀሳፊነቱ

355. ኤድስ በአብዛኛው የሚያጠቃው በወጣትነት የእድሜ ዘመናቸው ውስጥ ያሉትን ነው ሲል፡ ሀ. ስህተት ነው ሐ. የተጋነነ ነው

ለ.ትክክል ነው መ. በምንባቡ ውስጥ አልተጠቀሰም

356. ኤድስን ለመከላከል ዋናው መፍትሄ ምንድን ነው;

ሀ. በሀኪም የታዘዙትን መድኃኒቶች መጠቀም ሐ. ተከታታይ ማድረግ

ለ. ባህላዊ ኃይማኖታዊ ተፅእኖዎችን መቋቋም መ. የአመለካከትና የባህሪ ለውጥ ማምጣት

357. የኤድስ በሽታን ለመግታት በሚደረግ ዘመቻ ህዝብን ለማስተማር ከፍተኛ ድርሻ የተሰጠው ለማን ነው።

ሀ. ለመገናኛ ብዙኃን ሐ. ለወላጆች

ለ. ለትምህርት ቤቶች መ. ለመንግስት መስሪያቤቶች

358. የኤድስ ወረርሽኝ በተመለከተ በአለማችን እንደግንባር ቀደም መፈክር የሚጠቀሰው አባባል የቱ ነው; ሀ. ህብረተሰብ ያሸፋል

ለ. የሁላችንም ያላሰለሰ ጥረት ያስፈልጋል

ሐ. የለውጥ ሂደት የሆነው ወጣት ጋር አለም በኤድስ ይነሳል መ. ኤድስ ሰደድ

እሳት ነው

359. "ጅማሮ ተስፋ ሰጪ ነው" የሚለው ማንን ነው;

ሀ. ኤድስ በሀገራችን እያደረሰ ካለው ጉዳት አንፃር ያለውን ችሎታ ነው ለ.ኤድስን ለመከላከል

የሚደረገው ቅንጅታዊ አሰራር ነው

ሐ.የኤድስ ህሙማንን ቁጥር መቀነሱን ነው

መ. ከ41 ሚሊዮን ህሙማን 14 ሚሊዮን ያህሉ መሞታቸው ነው

360. "ያላሰለሰ ጥረት" ለሚለው ሀረግ በፍቺ ተመሳሳይ______________________ ነው;

ሀ. የማያቋርጥ ትግል ሐ. ከጊዜ ወደ ጊዜ

ለ. መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ መ. ግንባር ቀደም ሚና

361. ኤድስ በሀገራችን የልማት እንቅስቃሴ ላይ የሚያስከትለውን ችግር ቀላል የማይባልበት ምክንያት ምንድን ነው;

ሀ. በህዝብ ላይ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ተፅእኖዎች በማየላቸው ነው ለ. የኤድስ ቫይረስ

ተሸካሚ ቁጥር በጣም ብዙ በመሆኑ ነው

ሐ. በሽታው በአብዛኛው የሚያጠቃው ጎልማሶችንና አምራች ኃይሎችን በመሆኑ ነው መ. ኤድስ እንደሰደድ

እሳት በመዛመት ላይ በመሆኑ ነው

362. "እጥፍ ድርብ" የሚላቸው ምንድን ናቸው;

ሀ. ኤድስና ቫይረስ ለ. ስቃይና ሞት ሐ.ሞኝነትና ራስን ማታለል መ. ደዌና በሽታ

363. "ላፍታ እንኳ" ሲል______________________ማለቱ ነው;

ሀ. ለጥቂት ጊዜ ለ. በያመቱ ሐ. ዘወትር መ. በየስፍራው

364. ኢትዮጵያን በተመለከተ ስለ ኤድስ በመጀመሪያ አንቀጽ የተዓፈው_______________ነው። ሀ.

ቀደም ሲል የተደረገው እንቅስቃሴ አጥጋቢ አለመሆኑ

ለ. ትምህርት እየተሰጠ መሆኑን ሐ.

ህብረተሰቡ የነቃ መሆኑን

መ. የህሙማን ቁጥር ብዙ አለመሆን

365. ለምንባቡ ይበልጥ ተስማሚ ሊሆን የሚችል ርዕስ የትኛው ነው;

ሀ. ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴ

ሐ. ጨፍጫፊ በሽታ

ለ. ኤድስን በህብረት መከላከል

መ. መገናኛ ብዙኃን

**መመሪያ ሰላሳ ሁለት፡-ከተራ ቁጥር 366-392 ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

366. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች መካከል ትክክለኛ የአያያዥ ቃል አጠቃቀም የሚታይበት የትኛው ነው; ሀ. መሰረት ከውጭ ሀገር

ዛሬ ቢሆን ነገ ትመጣለች

ለ. አባይ ብዙ ዘመን ሸፍቶ ቆየ ይሁን እንጂ የህዝብ ጥሪ ሰምቶ ተመለሰ ሐ. ልጁ በፅኑ ታሟል

አለበለዚያ ሀኪም ቤት መሄድ አለበት

መ. ተማሪው ሌት ተቀን አጠና ነገር ግን ፈተናውን አለፈ

367. የልጁ ጠባይ በጣም አስቸጋሪ ነው_______________መክረን መመለስ አለብን። በዚህ ዐ.ነገር ውስጥ ባዶ ቦታውን በትክክል ሊያሟላ የሚችለው አያያዥ ቃል የትኛው ነው;

ሀ. ምክንያቱም ለ. አለበለዚያ ሐ. ቢሆንም መ. ከዚህም በላይ

368. ለክርክር ዝግጅት ትኩረት የሚሰጠው ከሚከተሉት መካከል ለየትኛው ነው; ሀ. የመከራከሪያ

ሀሳቦችን ከተከራካሪው አፍ መልቀም

ለ. ለክርክር የሚበጁ መረጃዎችን መሰብሰብ

ሐ. ለተከራካሪዎች የአሸናፊነት ፊት አለመስጠት መ. ተከራካሪዎችን

ማድነቅና ሀሳባቸውን መቃረን

369. እውቀትን ወይም ሀሳብን ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ የሚቻለው ከሚከተሉት በየትኞቹ የቋንቋትምህርት ክሂሎች ነው;

ሀ. በማንበብና ማዳመጥ

ሐ. በመናገርና ማንበብ

ለ. በመናገርና መፃፍ

መ. በማዳመጥና በመናገር

370. ከሚከተሉት ቃላት መካከል ጠብቆና ሳልቶ ሲነበብ ትርጉም የሚሰጠው የትኛው ነው; ሀ. ገብስ ለ. ቃጭል

ሐ. ጥፍር መ. መቀስ

371. ሰብሉ አረም እስኪውጠው ለምን ይጠበቃል; በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ ከተሰመረበት ሀረግ ጋር ትርጉም የሚመሳሰለው ከሚከተሉት የትኛው ነው

ሀ. እስኪያስቀምጠው ለ. እስኪያጠልቀው ሐ. እስኪያፍነው መ. እስኪሸፍነው

372. የሰው ልጅ ወደ ህይወት የመጣው በራሱ ምርጫ አይደለም ፤____________ህይወት የራሷ ምርጫ ስላላት። በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ ያለው ባዶ ቦታ በትክክል ማሟላት የሚችለው አያያዥ ቃል ከሚከተሉት የትኛው ነው;

ሀ. ምክንያቱም ለ.ስለዚህ ሐ.አለበለዚያ መ.እንዲሁም

373. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች መካከል የተውሳከ ግስ ቃል ተሳክቶ የሚገኘው በየትኛው ውስጥ ነው; ሀ. መፅሀፍ ማንበብ እውቀትን ይጨምራል

ለ. የገበሬው ግቢ በውሻ ይጠበቃል ሐ.ትምህርት ቤት

ቢዘጋም እንደገና ይከፈታል መ. ብዙ ሰዎች በእግር ኳስ

ጨዋታ ይዝናናሉ

374. ፈሪ ጨነቀው ተርበደበደ ጥይት

ዘነበ እሳት ወረደ ውረድ እንውረድ

ተባባሉና አስደበደቡት አፋፍ ቆሙና

የሚለው ግጥም ከሚከተሉት የስነ-ቃል ዘርፎች መካከል ለየትኛው ተስማሚ ነው; ሀ. ሙሾ ለ. ልመና

ሐ .እንጉርጉሮ መ.ፉከራ

375. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች መካከል ጥገኛ ሐረጎች በትክክል ተሰምሮበት የሚታየው የትኛው ነው; ሀ. መምህሩ እንደገባ ተማሪዎቹ ፀጥ አሉ

ለ. በሩን ልትዘጋ ስትሄድ ወደቀች

ሐ. ከመርካቶ የተነሳው አውቶቢስ ዘግይቶ ደረሰ መ. ጠረጴዛው ላይ የነበረው ሰዓት ወድቆ ተሰበረ

376. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በእውነታ ይዘት ላይ ያልተመሰረተው የትኛው ነው;

ሀ. ደብዳቤ ለ. ማስታወቂያ ሐ. ልብወለድ መ. የህይወት ታሪክ

377. ትረካው ገላጭ ነው ለማለት ይቻላል__________ምስል አለው__እንቅስቃሴ እናያለንድምፅ እንሰማለን _በአጠቃላይ የገፀ-ባህሪውን ስሜት እንጋራለን። በዚህ ዐ.ነገር ውስጥ የሚገኙ ባዶ ቦታዎች መግባት ያለበት ስርዓተ ነጥብ ከሚከተሉት የትኛው ነው።

ሀ. ፤ ለ. ፥ ሐ.። መ.!

378. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች መካከል የጥያቄ ምልክት የሚያስፈልገው የትኛው ነው; ሀ. ጓደኛዬን እንዴት
ይቅርታ እንደምጠይቀው አላውቅም
ለ.ጓደኛዬ እንደተቀየመኝ አውቃለሁ
ሐ. ጓደኛዬ ማን እንደሆንኩ አልተረዳኝም መ. ጓደኛዬን
እንዴት ይቅርታ ልጠይቀው

379. ውሃውን <u>ዢቅ አደረኩት</u>። በሚለው ዓ.ረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ወይም ሀረግ ትርጉም የትኛው ነው;

ሀ. አፈሰስኩት ለ.አስነካሁት ሐ.አመናጨሁት መ. አርከፈከፍኩት

380. ከገበያ የገዛችው ቲማቲም ስለተበላሸ ጣለችው። በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ የሚገኙትን ግሶች እንዲያስሩ ያደረጉት
መስተፃምሮች ከሚከተሉት መካከል የትኞቹ ናቸው;

ሀ. ከ፣የ ለ. የ፣ስለ ሐ. ከ፣ስለ መ. ከ፣ወ

381. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች መካከል ድብልቅ ዐ.ነገር የሆነው የትኛው ነው;
ሀ. ዝናቡም ስለዘነበ ፣ደጁም ስለጨቀየና ጎርፍም ስለሆነ መውጣት አልቻለም ለ. ዝናቡም ዘነበ ፣ደጁም
ጨቀየ፣ጎርፍም ጎረፈ፣ እንዴት ልውጣ
ሐ. ዝናቡ ፣ ጭቃና ጎርፍ ከቤት አያስወጣም
መ. የክረምት ዝናብ አካባቢውን ጭቃ በጭቃ፣ ጎርፍ በጎርፍ አደረገው

382. ከሚከተለው ተዘበራርቀው የተፃፈ ስለህይወት ታሪክ አፃፃፍ የሚገልፁ ሀረጎችን በጊዜ ቅደም ተከተል በትክክል
የሚያሳየው አማራጭ የትኛው ነው;

ሀ. የትምህርት ቤት ህይወት
መ. የተገኙ ሽልማቶች
ለ. በህይወት ዘመን የተከናወነ ተግባር
ሠ. የአስተዳደግና የቤተሰብ ሁኔታ
ሐ.የትውልድ ዘመንና ቦታ

ሀ. ሀ፣ ሠ ፣ለ፣ሐ፣ መ ሐ. ሐ፣ ሀ፣ሠ ፣ለ፣መ
B. ሐ፣ ሠ ፣ሀ ፣ለ፣መ መ. ሐ፣ ሀ፣መ፣ለ፣ሠ

383. ገመደ ፣ገማመደ፣ አገማመድ ፣ ገመድ በሚለው የቃላት ቅርፅ አለዋወጥ መሰረት ተፅፎ የሚገኘው ከሚከተሉት የትኛው
ነው;
ሀ. ለወጠ፣ ለዋወጠ፣ አለዋወጥ ፣ለዋጭ ለ. ነገረ፣
ነጋሪ፣ አነጋጋሪ ፣ነገር
ሐ. ገመጠ፣ ገማመጠ ፣አገማመጥ ፣ ገማጭ መ.
ሰፋሪ፣ ሰፋፈረ፣ አሰፋፈር፣ ሰፈር

384. በአንድ ፅሁፍ ውስጥ የአንድ ሰው፣ ስም የተወለደበት ቦታ ፣ትምህርቱ ፣ የፈፀማቸው ጉልህ ተግባራት… ከተገለፀ ፅሁፉ ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ሊሆን ይችላል;

ሀ. ልብወለድ ለ. የጉዞ ታሪክ ሐ. የህይወት ታሪክ መ. የጉዞ ማስታወሻ

385. "ልጁ ምሳውን በላ። ልጁ አሁን እጁን ይታጠባል። ልጁ ወደ ትምህርት ቤት ከሰዓት በኃላ ይሄዳል።" በዚህ ትምህርተ ጥቅስ ውስጥ የተፃፉት ሶስት ዐ.ነገሮች የተፃፈበት ጊዜ ቅደም ተከተል በትክክል የያዘው አማራጭ የትኛው ነው;

ሀ. የአሁን ጊዜ፣ የትንቢት ጊዜ፣ የሀላፊ ጊዜ ለ. የአላፊ ጊዜ፣

የአሁን ጊዜ ፣የትንቢት ጊዜ ሐ.የትንቢትጊዜ፣ የአሁን ጊዜ፣

የሀላፊ ጊዜ መ.የአሁን ጊዜ፣ የሀላፊ ጊዜ፣ የትንቢት ጊዜ

386. እኔና አንተ እነሱንና እሷን እንገናኛለን። በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ በሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ፣ ተባዕታዊ ፆታ የተገለፀው ተውላጠ ስም የትኛው ነው?

ሀ. እኔ ለ.እሷ ሐ.አንተ መ. እሱ

387. ከሚከተሉት አባባሎች መካከል ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ለሆነ ባለቤት የተነገረው የትኛው ነው; ሀ. መቼ መጣሽ ሙሽራ

መች ቆረጠምሽ ሽምብራ

ለ. አለማፈራ አንተን ማርከፍከፌ

ሐ. እንኳን ዘንቦብሽ እንደውም ጤዛ ነሽ መ. ራት

የላት ምሳ አማራት

388. ተማሪው ለትምህርቱ ያለው <u>ጉጉት</u> ጨምሯል። በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ የተሰመረበትን ቃል የሚመሳሰለው የትኛው ነው;

ሀ. ጥረት ለ.ፍላጎት ሐ.ክንውን መ.ህልም

389. ውስጣዊ ደስታ ለሰዎች መልካም ነገር በማድረግ <u>የሚፈጠር</u> ነው በዚህ ዐ.ነገር ውስጥ ለተሰመረበት ቃል ተቃራኒ ፍቺ የሚሆነው የትኛው ነው;

ሀ. የሚመነጭ ለ.የሚጎዳ ሐ.የሚጎመራ መ.የሚጠፋ

390. ወቅቱ የምርት መሰብሰቢያ ስለነበር <u>ትንፋሽ</u> አላገኘንም። በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ ምንድ ነው;

ሀ. ፋታ ለ.አየር ሐ.ጤና መ.ሰላም

391. ክብሮም <u>ሳተና</u> ነው። በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ ለተሰመረበት ቃል ተቃራኒ የሚሆነው ቃል የትኛው ነው;

ሀ. ቀርፋፋ ለ.ፈጣን ሐ.ክቡር መ.ተንኮለኛ

392. ዛሬ የበላሁት ምሳ በጣም ይጣፍጣል። የሚለው ሀተታዊ ዐ.ነገር ወደ ጥያቄያዊ ዐ.ነገር ሲቀየር የትኛውን ቅርፅ ይይዛል;

ሀ. ዛሬ የበላሁት ምሳ ጣፋጭ ነበር ለ.ዛሬ

የበላሁት ምሳ ለምን ጣፈጠ ሐ.ዛሬ የበላሁት ምሳ

በጣም ይጣፍጣል መ.ዛሬ የበላሁት ምሳ

አይማፍጥም

**መመሪያ ሰላሳ ሶስት፡-ከተራ ቁጥር 393-396 ከቀረቡት ልዩ ልዩ ጥያቄዎች አማራጭ ቀርበዋል ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ**

393. ፋጡማ በዝግታ ትራመዳለች። በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ተቃራኒ ፍቺ የቱ ነው; ሀ. በቀስታ ለ.በኩራት

ሐ.በፍጥነት መ.በመጀነን

394. አላዛር ቸር ልጅ ነው። በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ተቃራኒ-----------------------------ነው;

ሀ. የዋህ ለ.ኩሩ ሐ.ቆፍጣና መ.ትጉህ

395. መሰረት እያደር ኮሰሰች። በሚለው ዐ.ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ተቃራኒው ____________ነው። ሀ. ወፈረች

ለ.መነመነች ሐ.ከሳች መ.አረጀች

396. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች ውስጥ በመንስኤና ውጤት የተያያዘ ሀሳብ ያለው የትኛው ነው;

ሀ. ተቀምጦ አገኘሁት ለ.ቀና ብላ ቆመች ሐ.ተናደሽ አትመገቢ መ.ስላጠናሁ አለፍኩ

**መመሪያ ሰላሳ አራት፡- ከተራ ቁጥር 397 - 399 ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ምረጡ**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 397.ህልም | ሀ. እውን | ለ.ምኞት | ሐ.ተስፋ | መ.ትንቢት |
| 398.ማጥላላት | ሀ. ማዋረድ | ለ.ማሞገስ | ሐ.መመቸት | መ.ማጫወት |
| 399.ጣዕመ-ቢስ | ሀ. ለዛ -ያለው | ለ.ለዛ-ቢስ | ሐ.አሰልቺ | መ.የማይጥም |

**መመሪያ ሰላሳ አምስት፡-400- 402 ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ምረጡ።**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 400.አኳያ | ሀ. አንፃር | ለ.ተፎካካሪ | ሐ.በኩል | መ.ተወዳዳሪ |
| 401.ታጋሽ | ሀ. አስተዋይ | ለ.ቻይ | ሐ.ትሁት | መ.አዋቂ |
| 402.ሩህሩህ | ሀ. ትሁት | ለ.የዋህ | ሐ.አዛዛኝ | መ.ርግብ |

**መመሪያ ሰላሳ ስድስት፡-ግጥሙን በትኩረት ካነበባችሁ በኃላ ለእያንዳንዱ ጥያቄዎች ከቀረቡት አማራጮች መካከል ተገቢውን መልስ ምረጡ።**

አለሙን ጠፍጥሬ ቂጣ በጋገርኩት

ውኃውን ጨምቄ ቅቤ____________

ባወጣሁት ቅቤ ቂጣውን አርሼ ጨጩብሳ
ጭብጦ አድርጌ ለውሼ አንዴ በገጠምኩት
አንጀቴን ባራስኩት ምኞት ፈረስ ሆኖ የሽምጥ
አይሔድም
ደንገላሳ አይመታም ሶምሶማ አይረግጥም በህግ በተፈጥሮ
በታሪክ ስራቱ
አለም እንደወትሮ አለም እንደጥንቱ

**ምንጭ የኢትዮጲያ ደራሲያን ማህበር *1990* የዘመን ቀለማት ግጥም መድብል ቅፅ *1* ከገፅ*19* ተመጥኖ የተወሰደ**

403. ከላይ በቀረበው ግጥም ከሚከተሉት ሀሳቦች የትኛውን ያጠናክራል;

ሀ. ምኞት አለ ተግባር ዋጋ ቢስ ነው ሐ. ምኞት የህይወት መሻሻልን ያስገኛል

ለ.ምኞት ከተፈለገው ግብ ያደርሳል መ. ምኞት አንጀት ያደርሳል

404. ግጥሙ በስንት ስንኞችን እና ሀረጎች የተገነባ ነው;

ሀ. በ8 ስንኞችና በ16 ሀረጎች ሐ.በ10 ስንኞችና በ18 ሀረጎች

ለ. በ9 ስንኞችና በ18 ሀረጎች መ.በ9 ስንኞችና በ17 ሀረጎች

405. የግጥሙ ደራሲ በግጥም ውስጥ ምኞትን ለመግለፅ በዋነኝነት የተጠቀመበት ቃል ምንድነው; ሀ. ቅቤ ለ.ዓለም

ሐ.ተፈጥሮ መ.ፈረስ

406. ገጣሚው ማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት ከሚከተሉት መካከል የትኛው ነው; ሀ. ምኞት የተፈጥሮ ህግጋትና የህይወት ገፅታን መለወጥ ይችላል

ለ. ምኞት የአስተሳሰብን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያገለግል መሳሪያ ነው ሐ. ምኞት የተፈጥሮ ህግጋትንም ሆነ አለምን መለወጥ አቅም አለው

መ. ምኞት ቅቤ ያስበላል፤ አንጀት ያርሳል፤ ሆድ ይሞላል

407. በሁለተኛው ስንኝ የተተወው ባዶ ቦታ ላይ ቢገባ የግጥሙ ሀሳብና ምጣኔ የተሟላ የሚያደርገው ከሚከተሉት የትኛው ነው;

ሀ. ባወጣሁት ለ. በተቀባሁት ሐ. ጠጣሁት መ. በነካሁት

408. ከሚከተሉት ሀረጎች ወይም ዐ.ነገሮች መካከል የማወዳደር ስልት የሚታይበት የትኛው ነው; ሀ. መሬቱን ሰማይ ተደፋበት ሐ. ከቤቱ በላይ ያለው ዋርካ

ለ. ንግድና ግብርና መ. በእግር በፈረስ አሯሩጠው ያዙት

409. ከላይ ቀረበው ግጥም ስንት ስንኞች አሉት;

ሀ. ሰባት ለ. ስድት ሐ. ዘጠኝ መ. አስራ ሁለት

410. "ከሳሽ አቤቱታውን **<u>ከመሰረቱ</u>** ለማስረዳት የሚያስችሉትን ዝርዝር ሃሳቦቹን አከታትሎ አቀረበ።" በሚለዉ ዓ/ነገር ዉስጥ የተሰመረበት ቃል አዉዳዊ ፍች ከሚከተሉት በአንዱ ይገለጻል።

ሀ) ከእያንዳንዱ ለ) ከምንጨ ሐ) ከበርካቶች መ) ከማይስማማዉ

411. ከሚከተሉት አንዱ የንግግር ዝግጅት መመሪያ ዉስጥ አይመደብም። ሀ) ርዕሱን መረዳት

ለ) መረጃ መሰብሰብ

ሐ) የተሰበሰበን መረጃ እዉነትም ይሁን ሐሰት በማስረጃነት መጠቀም መ) ንግግሩ በተፈቀደለት የጊዜ ገደብ እንዲያልቅ መለማመድ

412. የሚከተሉትን ዓ/ነገሮች የተስተካከለ አንቀፅ ይሆን ዘንድ መቅረብ ያለባቸዉ በየትኛዉ ቅደም ተከተል ነዉ?

፩) የማርፍበት አዘጋጅታልኝ ነበር።

፪) ጎንደር ከደረስኩ በኋላ ከአዉቶብስ ወረድኩና ወደ አያቴ ቤት አመራሁ።

፫) ጥቂት እንዳረፍኩ የአጎቴን መኖር ጠየኳት።

፬) አያቴ በደህና ተቀበሉኝ።

፭) ለሥራ ወደ ባህርዳር መሄዱን ነገረችኝ።

ሀ) ፪፣፬፣፫፣፩፣፭ ለ) ፩፣፭፣፬፣ ፫፣፪ ሐ) ፪፣፬፣፩፣፫፣፭ መ) ፪፣፫፣፭፣፩፣፬

413. "አስባለሁ" የሚለዉ ቃል መደቡ ፣ ቁጥር እና ጾታዉ ____________________ ፣_________ እና________ ነዉ።

ሀ) ሦስተኛ፣ነጠላ፣አይለይም ሐ) አንደኛ፣ብዙ፣አይለይም

ለ) አንደኛ፣ነጠላ፣አይለይም መ) ሦስተኛ፣ብዙ፣አይለይም

414. አራቱ የቋንቋ ክሂሎች እንደ ቅደም ተከተላቸዉ ሲቀመጡ ከሚከተለዉ ትክክለኛዉ ቅደም ተከተል የትኛዉ ነዉ?

ሀ) መጻፍ፣መናገር፣ማዳመጥ፣ማንበብ ለ) መናገር፣መጻፍ፣ማዳመጥ፣ማንበብ ሐ) ማንበብ፣መጻፍ፣ማዳመጥ፣መናገር መ) ማዳመጥ፣መናገር፣ማንበብ፣መጻፍ

415. ከሚከተሉት አራት ምርጫዎች አንዱ በትርጉምም ሆነ ቃሉ ከሚጠራቸዉ ጉዳዮች የተለየ ነዉ። ሀ) ማር ለ) ሰም ሐ) ሰፈፍ መ) እንኳይ

416. "የአካሏ ዉበት ፣ ወዟና ጠይምነቷ **ወከክ ያደርጋል**፡፡" የተሰመረበት ሐረግ ትርጉም የሚሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ) ልብ ይሰረስራል ሐ) ልብ ይለበልባል

ለ) ልብ ይሰነጥቃል መ) ልብ ይበረብራል

417. ልጁ ጥቂት **ካጣጣረ** በኋላ ተጠናቀቀ፡፡ የተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍቹ _______ ነዉ፡፡ ሀ) ሞተ ለ) ተጠንቅቆ ሞተ ሐ) ዝግጁ ሆነ መ) ጥንቃቄ አደረገ

418. ናትናኤል የትምህርት **ፍላጎቱ** ዝቅተኛ ነዉ፡፡ ለተሠመረበት ቃል ፍቺ የሚሆነዉ የቱ ነዉ? ሀ) ጭንቀቱ ለ) ዕቅዱ ሐ) ጥረቱ መ) ዝንባሌዉ

419. አንደበተ ርቱዕነት ከቋንቋ ክሂሎች መካከል ከየትኛዉ ጋር አብሮ ይሄዳል?

ሀ) ከመጻፍ ለ) ከማንበብ ሐ) ከማዳመጥ መ) ከመናገር

420. በአንድ ቅኔ ዉስጥ ወርቅ የምንለዉ

ሀ) ምስጢሩን ነዉ ሐ) ፈርጥ ስለሆነ ነዉ

ለ) በሰም የተሸፈነዉን ነዉ መ) ሀ እና ለ

**መመሪያ ሰላሳ ሰባት፡- ከጥያቄ 421 እስከ 4ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

አንድ ሀሳብ ከአእምሮ ወደ ፅህፈት በመቀየሩ ብቻ ፀሀፊው ወደ ተደራሲው ተላልፎ መግባባትን ይፈጥራል ማለት አያስደፍርም፡፡ የታሪክ ምርምር ሊቃውንት ከአንዳንድ ሀገሮች ታሪካዊ ድርጊት የተፈፀመባቸውን ቦታዎች በመቆፈር የተለያዩ ፅሁፎችን ለማግኘት በቅተዋል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ሊቃውንት እስካሁን ድረስ አንዳንዶቹ ፅሁፎች የያዙትን ሀሳብ መረዳት አልቻሉም፡፡ የዚህ ዋናው ምክንያት የዛሬዎቹ ሊቃውንት ፅሁፎችን ማንበብ ባለመቻላቸው ነው፡፡ ስለዚህ እንዲህ ያሉት ቋንቋዎች መግባቢያ መሳሪያነታቸውን በጊዜው ለነበሩ ሰዎች ብቻ ነው፡፡ ፅሁፎችን ማንበብ እስካልተቻለ ድረስ ፅሁፎች ከላንቲካነት አልፈው ለመግባቢያነት ሊጠቅሙ አይችሉም፡፡

በዛሬው ዘመንም ቢሆን የተለያዩ ህዝቦችን የፅሁፍ ቋንቋዎች ሁሉ ማንበብ የሚችል ሰው የለም፡፡ እርግጥ አንድ ሰው ሁለትና ሶስት ከዚያም አለፈ ቢባል ከአምስት እስከ አስር የተለያዩ ቋንቋዎችን ማንበብም ፣ መናገርም ይችል ይሆናል፡፡ ባንፃሩ ደግሞ በገዛ አገሩ የሚነገሩትን ከሰባ እስከ ሰማንያ የሚደርሱ ቋንቋዎችን አንብቦም ሆነ ሲነገሩ ሰምቶ መረዳት የሚችል አለ ለማለት ያዳግታል፡፡

ቀደም ብሎ እንደተጠቆመው፣ በፅሁፍ የሰፈረ ሀሳብ በፅሑፍ በመገለጡ ብቻ የመግባቢያ መሳሪያ ሊሆን አይችልም፡፡ በምንናገረው ቋንቋ የሰፈሩ አንዳንድ ሀሳቦች እንኳን የፍቺያቸውን እጅና እግር

ለመለየት ብዙ ጊዜ ይሳነናል፡፡ ይህ ከሚሆንባቸው ምክንያቶች ዋናዎች በፅሁፍ የቀረበው ሀሳብ በማናውቃቸው ቃላት የተቀናበረ ሲሆን ወይም ደግሞ ቃላቱ ራሳቸው የተሳኩበት ሁኔታ ሀሳቡን በማጉላት ፋንታ የሚያደምኑ ሲሆኑና የሐሳብ አቀራረብ የማይጥምና የማይስብ ሆኖ ሲገኝ የመልዕክቱን ተቀባይ ፍላጎት በመግታት ሀሳቡን እንዳይቀስም ያግዱታል፡፡ አንድ ሀሳብ በፅሁፍ የሚገለጥበት ጊዜ ከፍ ብለው ከተጠቀሱት እክሎች ነፃ ካልሆነ የመግባቢያ መሳሪያነቱ እምብዛም ይሆናል፡፡

(አማረ ማሞ ፣ የኢልቦለድ አጻጻፍ ገፅ 11 — 12)

421. የመግባቢያ መሳሪያነቱ እምብዛም ይሆናል ሲል ምን ማለቱ ነው? ሀ. መልዕክቱን በተፈለገው መንገድ ያስተላልፋል፡፡

ለ. መልዕክቱን ማስተላለፍ የማይቻልበት ደረጃ ላይ ይደረሳል፡፡ ሐ. በተፈለገው ሁኔታ መልዕክቱን ማስተላለፍ አይችልም፡፡ መ. ለመግባቢያ የሚሆነው መሳሪያ በበቂ ሁኔታ አይገኝም፡፡

422. የፍቺያቸውን **<u>እጅና እግር</u>** ለመለየት ብዙ ጊዜ ይሳነናል፡፡ የተሰመረበት ሐረግ ትርጉም ________________________ነው?

ሀ. የሰውነት ክፍል ሐ. ከላይና ከታች

ለ. ትክክለኛ ትርጉም **መ. መልሱ አልተሰጠም**

423. ከላይ የቀረበው ምንባብ ተስማሚ የሚሆነው ርዕስ የትኛው ነው?

ሀ. ፅሑፍና መግባባት ሐ. የምንፅፍበት ምክንያት

ለ. የፅሁፍ ደካማ ጎን **መ. ሁሉም መልስ ናቸው**

424. ከመግባቢያነቱ ይልቅ **<u>ውዥንብር አሰራጭነቱ</u>** የጎላ ሊሆን ይችላል፡፡ የተሰመረበት ሀረግ ትርጉሙ ___________________**ነው?**

ሀ. መልዕክት አስተላላፊነት ሐ. አደናጋሪነት ማስፋፋቱ

ለ. የመልዕክቱን ግልፅነት **መ. ተደማጭነት ማግኘቱ**

425. ፍላጎቱን በመግታት ሀሳቡን **<u>እንዳይቀስም</u>** ያግዱታል፡፡ የተሰመረበት ቃል ትርጉም _______________________ነው?

ሀ. እንዳይወስድ ለ. እንዳያነብ ሐ. እንዳይረዳ መ.መልሱ አልተሰጠም

426. በሦስተኛው አንቀፅ ላይ ቀደም ብሎ እንደተጠቀመው የሚለው ሀረግ የሚጠቁመው የትኛውን ጊዜ ነው?

ሀ. በ1ኛውና በ2ተኛው አንቀፅ ላይ የሰፈረውን ሀሳብ፡፡

ለ. ከሃያ እና ከሃያ አምስት አመታት በፊት ያለውን እሳቤ፡፡ ሐ. ጥቆማው ግልፅ አይደለም፡፡

**መ. ሁሉም መልስ ነው፡፡**

427. ________________ ታሪካዊ ድርጊት የተፈፀመባቸውን ቦታዎች **በመቆፈር** ሲል የተሰመረበት ቃል ትርጉም_ ________________ ነው

ሀ. በማመስ ለ. በመጎርጎር ሐ. በመፈለግ መ. ሁሉም

428. ________________ ፅሁፎች ከላንቲካነት አልፈው ለመግባቢያነት ሲጠቅሙ አይችሉም ሀ. ፅሁፍ ሁሉ አይጠቅምም ማለቱ ነው፡፡

ለ. ፅሁፍ ለጌጥነት ሊያገለግል ይችላል ማለቱ ነው ሐ. አንድ ፅሁፍ ካልተነበበ ዋጋ የለውም ማለቱ ነው፡፡

መ. ምንም ቢሆን ፅሁፍ መጥቀሙ አይቀርም ማለቱ ነው፡፡

429. በፅሁፍ የሰፈረው ሀሳብ በፅሁፍ **በመገለጡ** ብቻ ሲል የተሰመረበት ሀረግ ትርጉሙ ______________ ነው፡፡ ሀ. በመታየቱ ለ. ባለመሸፈኑ ሐ. በመገኘቱ መ. ሁሉም

430. ከፍ ብለው ከተጠቀሱት **እክሎች** ነፃ ካልሆነ ሲል የተሰመረበት ቃል ትርጉም____________________ ነው፡፡

ሀ. ጉዳይ ለ. ችግር ሐ. ስቃይ መ. ሐዘን

## መመሪያ ሰላሳ ስምንት፡-ከጥያቄ 431 እስከ 31 ድረስ ላሉት ለእያንዳንዱ ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

431. ከሚከተሉት ዓ.ነገሮች መካከል በአውንታዊ የቀረበው የትኛው ነው? ሀ. ዝናቡ ወቅቱን ጠብቆ አልዘነበም፡፡

ለ. በጋራ ሰርቶ በጋራ መጠቀም የሚስገኘው ጥቅም አልታወቀም፡፡ ሐ. የሚጠበቅበትን ስላልሰራ የሚገባውን አላገኘም፡፡

መ. በጉጉት ሲጠበቅ የነበረው እንግዳ መጣ፡፡

432. ከሚከተሉት አረፍተ ነገሮች መካከል በአሉታ የተገለፀው ዓ.ነገር የትኛው ነው? ሀ. ትምህርት ቤት ልትሄድ ነበር፡፡

ለ. ትምህርት ቤት ትሄዳለች፡፡

ሐ. ትምህርት ቤት ሄዳ ይሆናል፡፡ መ. ትምህርት ቤት አልሄደችም፡፡

433. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ብዛትን የሚያመለክተው ቅጥያ ያልያዘው የትኛው ነው? ሀ. ልጆቻቸው

ለ. ነገረቻቸው ሐ. መሰቦቻቸው መ. ጎረቤቶቻቸው

434. ማዳመጥን አስመልክቶ አውንታዊ ሀሳብ ካላቸው መካከል የተለየው የትኛው ነው? ሀ. ጨዋታን አዳምጦ እህልን አላምጦ

ለ. ጆሮ የሰማውን ልብ ያውቃል ሐ. ያልሰማ ጆሮ ከጎረቤት ያጣላል

መ. የነገር ወጡ ማዳመጡ

435. እውቀትን ወይም ሀሳብን ለሌላው ሰው ለማስተላለፍ የሚቻለው ከሚከተሉት በየትኞቹ የቋንቋ ትምህርት ክሂሎች ነው?

ሀ. በማንበብና በማዳመጥ
ሐ. በመናገርና በማንበብ
ለ. በመናገር በመጻፍ
መ. በማዳመጥና በመናገር

436. "ኮበሌዎቹን" ጥራቸው በሚለው ዓ.ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል በምዕላድ ሲተነተን ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ሊሆን ይችላል?

ሀ. ኮበሌ - ዎች - ኡን
ሐ. ኮበሌ - ኦች - ን
ለ. ኮበሌ - ዎች - ኡ -ን
መ. ኮበሌ - ዎች - ን

437. "ወታደሩ ጠላቱን በጥይት ገለበጠው።" ከሚለው ዓረፍተ ነገር ጋር በቅርፅ ተመሳሳይ የሆነው ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?

ሀ. ሰርገኛ እየጨፈረ ከሙሽሪት ቤት ገባ።

ለ. ተማሪው በእግሩ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ። ሐ. ሴትየዋ

ሽንኩርቱን በቢላ ከተፈችው።

መ. ሾፌሩ መኪናውን እያሽከረከረ መጣ።

438. አንድ ተናጋሪ የአድማጮችን ማንነት በትክክል ተረድቷል የሚባለው ምን ሲያደርግ እንደሆነ የሚያመለክተው ከሚከተሉት አማራጮች የትኛው ነው?

ሀ. ንግግር በሚደረግበት ርዕስ ዙሪያ ለአድማጮች መረጃ ሲያሰባስብ

ለ. በንግግር ሂደት ውስጥ መረጃዎች አሰባስቦ ፣ አስተዋፅኦ ነድፎ ለአድማጭ ሲያቀርብ ሐ. ከአድማጮች እድሜ ፣ እውቀት ፣ ልምድና ችሎታ ጋር የተገናዘበ ንግግር ሲያቀርብ መ. ተናጋሪው ንግግሩን ከጠቃሚነት ፣ ከወቅታዊነት ፣ ከመስህበነት አንፃር አገናዝቦ

ሲያቀርብ

439. ቀጥሎ በቀረበው ዓ.ነገር መጨረሻ ላይ የሚገባው ስርአዓተ ነጥብ የትኛው ነው? እንግዲህ ጉራህን የነፋህበትን የፈጠራ ስራ እስቲ አናያለን

ሀ. ጥያቄ ምልክት
ሐ. ድርብ ሰረዝ
ለ. አራት ነጥብ
መ. ትእምርተ አንክሮ

440. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በምክንያትና ውጤቱን የያዘው ዓ.ነገር የትኛው ነው?

ሀ. ለመሄድ ተጣድፏል።
ሐ. ተማሪዎች በመማር ላይ ናቸው።
ለ. በመማራችን ተደስተናል።
መ. ዘወትር ትምህርቷ ታጠናለች።

441. በግርጌያቸው ከተሰመረባቸው ቃላት መካከል በእማሬያዊ ፍቺ የገባው የትኛው ነው።

ሀ. ሰናይት ያገባችው ባል **መልዓክ** ነው::

ለ. ትላንት በጎርፍ **ተራቁቶ** የነበረው ተራራ ዛሬ በዛፍ ተሸፍኗል:: ሐ. እሷ እንደሆነች **መሬት** ናት ያሏትን ሁሉ እሺ ነው የምትለው:: መ. ልጃችን ይኼው ዛሬ አድጎ ስንጣላ **ሽማግሌ** ሆኖ ያስታርቃል::

442. ከሚከተሉት ዓ/ነገሮች ትዕምርተ አንክሮ መጨረሻ ላይ የሚጠቀመዉ የቱ ነዉ? ሀ. ሀተታ ዓ/ነገር

ሐ. ትዕዛዛዊ ዓ/ነገር

ለ. ጥያቄያዊ ዓ/ነገር መ. አጋናኝ ዓ/ነገር

443. ሐሴት ለሚለዉ ቃል ተቃራኒ የሚሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ደስታ ለ. ፅልመት ሐ. ፍስሀ መ. ፍካት

444. ከሚከተሉት ቃላት መካከል የመጀመሪያ የሚለው ፍቺ የሚሰጠዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ቤዛ ለ. ቀየ ሐ. ጋለሞታ መ. በኩር

445. አራቱ የቋንቋ ክሂሎች እንደ ቅደም ተከተላቸው ሲቀመጡ የሚያመለክተው አማራጭ የቱ ነው? ሀ. መፃፍ ፣ መናገር ፣ ማዳመጥ ፣ ማንበብ

ለ. መናገር ፣ መፃፍ ፣ ማዳመጥ ፣ማንበብ

ሐ. ማንበብ ፣ መፃፍ ፣ ማዳመጥ ፣ መናገር መ. ማዳመጥ ፣ መናገር ፣ ማንበብ ፣ መጻፍ

446. ልጅቱ ለችግሯ **ቋሚ** መፍትሄ አገኘች። በሚለው ዓ.ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ዓውዳዊ ፍቹ የቱ ነው?

ሀ. ትንሽ ለ. ዘላቂ ሐ. የማይንቀሳቀስ መ. መጠነኛ

447. ተማሪዎቹ የተሰራውን ሥራ አላዩትም። ይህ ዓ.ነገር ከየትኛው ዓ.ነገር ይመደባል።

ሀ. አውንታዊ ለ. አሉታዊ ሐ. ትዕዛዛዊ መ. አጋኗዊ

448. ምላሽ የሚሹ ዓ.ነገሮች ወይም ማን? ለምን? መቼ? እንዴት? የመሳሰሉት ቃላትን በመጠቀም የሚመሰረት የዓ.ነገር ዓይነት የቱ ነው?

ሀ. መጠይቃዊ ለ. ትዕዛዛዊ ሐ. ሐተታዊ መ. አጋኗዊ

449. አዳኙ ጦሩን ----------------- ጥቅጥቅ ወዳለዉ ጫካ ገባ። ባዶ ቦታዉን የሚያሟላዉ ቃል የትኛዉ ነዉ?

ሀ. እየቀሰረ ለ. እየወደረ ሐ. እያነጣጠረ መ. እየሰበቀ

450. የድርሰት ዋና ሀሳብ የሚተላለፍበት የድርሰት ክፍል የትኛው ነው?

ሀ. ሀተታ ለ. መግቢያ ሐ. ርዕስ መ. መደምደሚ

451. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ትዕዛዛዊ ዓ.ነገር የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. እንዴት ያለች ቆንጆ ልጅ ናት!

ለ. መቼ እንደምትሄጅ አልነገርሽኝም?

ሐ. ከመፅሐፍ ቤት የወሰዳችሁትን መፅሐፍ መልሱ! መ. ድንቄም

ምንኩስና!

**ምንባብ**

ባህር ዳር ለክልሉ ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች ከፌደራል መንግስት በሚላኩ ባለስልጣናት ለአራት ቀናት የሚቆይ ስልጠና እንዳለና የመጀመሪያው ቀን ከጠዋቱ 2፡30 እንደሚጀመር ተነገረ። በዚህ መሰረት ሰልጣኙ ከየዞኑ ፣ ከክልል ቢሮዎችና ተቋማት ቢሮ እየተዘጋ ወደ ጉባኤ አዳራሽ ተመመ። በዐባይ ወንዝ ዳርቻ የተገነባውና የተንጣለለው የጉባኤ አዳራሽ ከ2፡30 ጀምሮ ጢም ብሎ ሞልቷል ሰልጣኙ ቢገኝም አሰልጣኞቹ ግን አንዱም ብቅ ያለ የለም ሶስት ሰዓት ተኩል ሆነ አሁንም የውሃ ሽታ ሆኑ።

ኋላ ላይ ከአስተባባሪዎቹ አንዱ ወደ መድረክ ወጣና "አሰልጣኞች ዛሬ ጠዋት ነው ከአዲስ አበባ በአውሮፕላን የገቡት እና ቁርስ ይቅመሱ ብለን ነው" አለ ከአዲስ አበባ በጠዋት ወደ ባህርዳር የሚመጣው የመጀመሪያው አውሮፕላን የሚደርሰው ጠዋት ሶስት ሰዓት ተኩል ነው ይታያችሁ ሰልጣኙ ግን አዳራሽ እንዲገኝ የተነገረው ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ነው በምትቀጥረው ሰዓት እንደማትገኝ እያወክ ቀድመህ መቅጠር ለሰዎች ያለህን ንቀት ከማሳየቱም በላይ እምነት እንዳይጣልብህ የሚያደርግ ይመስለኛል።

አሰልጣኞቹ ባህር ዳር ሲደርሱም ሰልጣኙ አዳራሽ ገብቶ እየጠበቀ መሆኑ እየታወቀ ቁርስ ሊቀምሱ ወደ ሆቴል መሄዳቸው ደግሞ የበለጠ ይገርማል። እርግጥ ቁርስ "ሊበሉ" ሳይሆን "ሊቀምሱ" ነው የተባለው ስለስልጣናቸው ሲባል ለትህትና ነው እንጂ እንደዚህ ያሉ ለሰው የማይጨነቁ ፍጡሮች እንኳን በመቅመስ በመብላት የሚመለሱ አይደሉም።

ወደ አራት ሰዓት ሲጠጋ አሰልጣኞቹ ወደ አደራሹ ሲገቡ በክብር ለመቀበል ተነሳን። ወደ አዳራሹ ሲገቡ ሰዓት አርፍደው እንደመጣ ሰው እየተሽቆረቆጡ ሳይሆን እየተንጎማለሉ ከፊት ክፍት ሆኖ ወደሚጠብቃቸው ቀይ ወንበር አመሩ። ድንቁርናችን ከመግዘፉ የተነሳ ነውራችን ክብራችን ሆነ፡ በመዘግየታቸው የተሰማቸው የህሊና ወቀስ ስለመኖሩ እጠራጠራለሁ።

*ምንጭ፡- ‘ሽበዝ” ዓለማየሁ ዋሴ እሸቴ (ዶ/ር)*

*ሚያዝያ 2012 ዓ.ም ገፅ 153*

***መመሪያ ሰላሳ ዘጠኝ፡-*** ***ከጥያቄ 1 እስከ 10 ድረስ የቀረቡት ጥያቄዎች በቀረበው ምንባብ የተመሰረቱ ናቸው ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሠጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጭ፡፡***

452. እንደ ምንባቡ አገላለፅ በስልጠናው ቦታ ቀድመው የተገኙት

ሀ. አሰልጣኞች ለ. ሠልጣኞች ሐ. አስተናባሪዎች መ. ሁሉም

453. ከአስተናባሪዎቹ አንዱ ለሠልጣኞቹ የነገራቸው ምንድነው

ሀ. የስልጠናው ሰዓት መራዘሙን ሐ. አሰልጣኞች ቁርስ ሊበሉ እንደሆነ

ለ. የስልጠናው ሰዓት በማለፉ ይቅርታ መ. የስልጠናው ቦታ

454. ይህ ምንባብ ------------------------- ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል

ሀ. ለህይወት ታሪክ ለ. ለአጭር ታሪክ ሐ. ለጉዞ ማስታወሻ መ. ሁሉም

455. በዚህ ምንባብ ፀሐፊው ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ምንድነው ሀ. ቀጠሮ አለማክበር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለመደ መምጣቱን

ለ. በጥፋታችን ከመፀፀት ይልቅ እንደ ክብር መቁጠር

ሐ. ሀ እና ለ መ. መልስ የለም

***መመሪያ አርባ፡-*** ***ከጥያቄ 456 እስከ 481 ድረስ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡***

456. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች አንዱ የመሆን ግስ በመጠቀም የተመሰረተ ነው፡፡

ሀ. ሽመልስ መፅሐፍ አነበበ፡፡ ሐ. አስቴር ቤት ሰራች፡፡

ለ. ሜሮን ደብተር ገዛች፡፡ መ. ዳዊት ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡

457. በአንድ ፅሁፍ ላይ ደራሲው የሚፈጥራቸው ባለታሪኮ ምን ተብለው ይጠራሉ

ሀ. መቼት ለ. ሀያሲ ሐ. ገፀ-ባህሪያት መ. ታዳሚ

458. አንድ ድርሰት ለመፃፍ ትክክለኛ የሆነው ቅደም ተከተል የቱ ነው

ሀ. አስተዋፅኦ መንደፍ ፣ ርዕስ መምረጥ ፣ ረቂቅ መፃፍ ፣ ፅሁፍ ማረም ለ. ርዕስ መምረጥ ፣ አስተዋፅኦ መንደፍ ፣ ረቂቅ መፃፍ ፣ ፅሁፍን ማረም ሐ. ረቂቅ መፃፍ ፣ ርዕስ መምረጥ ፣ አስተዋፅኦ መንደፍ ፣ ፅሁፍ ማረም

መ. ርዕስ መምረጥ ፣ አስተዋፅኦ መንደፍ ፣ ፅሁፍ ማረም ፣ ረቂቅ መፃፍ

459. ከሚከተሉት ቃላት ልዩ የሆነው የቱ ነው

ሀ. አምቡላ ለ. ሰፌፍ ሐ. ገፈት መ. ስልባቦት

460. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች መካከል በትክክለኛ ስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም የተፃፈው የትኛው ነው ሀ. ስምህ ማነው ብሎ ጠየቀኝ።

ሐ. "ስምህ ማነው ብሎ ጠየቀኝ።"

ለ. "ስምህ ማነው" ብሎጠየቀኝ።

መ. "ስምህ ማነው " ብሎ ጠየቀኝ።

461. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የውይይት አቀራረብ መመሪያ ያልሆነው የቱ ነው ሀ. የውይይቱን ርዕስና ዓላማ ለአድማጭ ማስተዋወቅ

ለ. ከውይይቱ ርዕስ ጋር ተያያዥነት የሌላቸው መረጃዎች ማቅረብ ሐ. ጎላ ባለድምፅና ስርዓት ባለው መንገድ መናገር

መ. በተሰጠው የጊዜ ገደብ ሐሳብን ማጠናቀቅ

462. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ግጥማዊ ቃላት የሚገልፀው የቱ ነው

ሀ. ረቂቁን ተጨባጭ ያደርጋል ሐ. ምትና ዜማን ይፈጥራል

ለ. እምቅ ሀሳብ ይይዛል **መ. ሁሉም መልስ ይሆናል**

463. ‹‹ልጁ ብርጭቆ ሰበረ። ልጁ ብርጭቆ እየሰበረ ነው። ልጁ ከሰዓት ትሌት ይሄዳል------------------ ፡፡እነዚህ የተጠቀሱ ሶት ዓ.ነገሮች ከጊዜ አንፃር ---------- ፣ ----------- እና---------------------------------- ናቸው።

ሀ. የሀላፊ ጊዜ ፣ የአሁን ጊዜ ፣ የትንቢትጊዜ ለ. የአሁን ጊዜ ፣ የአላፊ ጊዜ ፣ የአሁን

ሐ. የአሁን ጊዜ ፣ የትንቢት ጊዜ ፣ የአላፊ ጊዜ መ. የአላፊ ጊዜ ፣ የትንቢት ጊዜ ፣ የአሁን ጊዜ

464. ከሚከተሉት ዐ.ነገሮች መካከል የድርብ ዓ.ነገር ምሳሌ የሆነው የቱ ነው ሀ. እናትየው የልጇን ወደ ሸርሸር ቦታ ወሰደቻት።

ለ. አፈርና ውሃ ለኑሯችን አስፈላጊዎ ናቸው።

ሐ. ድሬዳዋ ከተማ ሞቃት የአየር ፀባይ አላት ፤ ነገር ግን ከሰዓት በኋላ ነፋሻ አየር ይነፍስባታል።

መ. ሐረር ወጣ ገባ የመሬት አቀማመጥ አላት።

465. ደራሲው በአንባብያን ዘንድ አድናቆትን ያተረፈ መፅሐፍ ደረሰ የተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍቺ የቱ ነው

ሀ. ፃፈ ለ. አቀረበ ሐ. ጠረዘ መ. አሳተመ

466. ከሚከተሉት ዓ.ነገሮች መካከል ጥገኛ መስተፃምር የያዘው የቱ ነው ሀ. ፋጡማና ጋሻው አብረው መጡ፡፡

ለ. አለማየሁ ሁለት ኪሎ ሙዝ ገዛ፡

ሐ. ንግስት ስራዋን በጥሩ ሁኔታ ታከናውናለች፡፡ መ. አህመድ ቶሎ ስለመጣ ደብተሩን አገኘ፡፡

467. ከሚከተሉት ዓ.ነገሮች መካከል ስለንባብ ትክክልኛ የሆነው የትኛው ነው ሀ. የሚነበቡ ነገሮች ተመሳሳይ የንባብ ስልት አላቸው

ለ. በዓላማ የሚነበቡ ፅሁፎች በአንድ ዓይነት የንባብ ስልት ይመራሉ ሐ. የንባብ ዓላማ የተለያዩ የንባብ ስልቶችን እንድንከተል ያደርጋል

መ. ማንኛውም የንባብ ስልት ፈተና ለማለፍ የሚረግ የአነባበብ ስርዓት ነው፡፡

468. "ያንን የታመመ ህፃን ባየሁ ቁጥር <u>አንጀቴን ይበላኛል</u>፡፡" በሚለው ዓ.ነገር ውስጥ የተሰመረበት ሀረግ ፍቺ ከሚከተሉት መካከል የትኛው ነው

ሀ. ያሳክከኛል ለ. ያሳዝነኛል ሐ. ያቁነጠንጠኛል መ. ያውከኛል

469. በሚከተሉት ዓ.ነገሮች ውስጥ ከተሰመረባቸው ቃላት ወይም ሀረጋት መካከል ጠቋሚ መስተዓምር የሆነውን የያዘው ዓ.ነገር ስንተኛው ነው

1. <u>ትልቁ</u> ልጅ የ3ደኛዋ ልጅ ነው፡፡
2. <u>የቡና</u> አፈላል ባህላችን ታዋቂ
3. <u>ስለታሪካችን</u> ማወቅ ተገቢ ነው፡፡
4. <u>ይህ</u> መፅሐፍ የእህቴ ነው፡፡

ሀ. አንደኛው ለ. ሁለተኛው ሐ. ሶስተኛው መ. አራተኛ

የበቀለች ወንድም <u>ኩራዝ</u> ነው፡፡ በዚህ ዓ.ነገር የተሰመረበት ቃል ፈሊጣዊ ትርጉሙ ምንድነው ሀ. አጭር ለ. ብርሃን

ሐ. ቀይ መ. ጠንካራ

470. "አየሩ በጣም ቀዝቃዛ ነው ፤ ----------- የሚሞቅ ልብስ መደረብ አለብኝ፡፡" በዚህ ዓ.ነገር ውስጥ መግባት ያለበት አያያዥ ቃል የቱ ነው

ሀ. ወይም ለ. እንጂ ሐ. ስለዚህ መ. ነገር ግን

471. የንግግር ሂደት መመሪያ ሀሳቦን ተዘበራርቀው ተፅፈዋል መመሪያዎች በየትኛው ቅደም ተከተል ይፃፋሉ

ሀ. ንግግር ሳቢና ማራኪ አድርጎ ማቅረብ

ለ. ለተጠየቁት ጥያቄዎ ገለፃ መስጠትና ማጠቃለል ሐ. በንግግር

መጨረሻ ምስጋና ማቅረብ

መ. የንግግሩን ዓላማ ማስተዋወቅ

ሀ. ሐ፣መ፣ለ፣ሀ ለ. ሐ፣መ፣ሀ፣ለ ሐ. መ፣ለ፣ሀ፣ሐ መ. መ፣ሀ፣ለ፣ሐ

472. የንግግር ችሎታን አዳብሮ ሰዎችን ለማሳመን ከሚከተሉት በየትኞቹ በቂ ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል። ሀ. ጽህፈት ፣ ሪፖርት ፣ ጥናት ሐ. ትረካ ፣ ሙገሳ ፣ ድራማ

ለ. ጭውውት ፣ ውይይት ፣ ክርክር መ. ንባብ ፣ ምርምር ፣ ትችት

473. ከሚከተሉት መካከል ከትንሽ ወደ ብዙ በሚል ቅደም ተከተል የተፃፈው የትኛው ነው ሀ. እፍኝ ፣ ጭብጥ ፣ እቅፍ

ሐ. ጭብጥ ፣ እቅፍ ፣ እፍኝ

ለ. እቅፍ ፣ እፍኝ ፣ ጭብጥ

መ. ጭብጥ ፣ እፍኝ ፣ እቅፍ

474. ‹‹አስጨረሳቸው የሚለው ቃል በመነጣጠል ለንድፍ----------------------ይሆናል

ሀ. አስጨሰሉቸው

ሐ. አስ-ጨረስ-ኣቸው

ለ. አስ-ጨረሳቸው

መ. አስጨረሰ-ኣቸው

475. ቅጣት” ለሚለው ቃል ተቃራኒ ፍቺ የሚሆነው የቱ ነው

ሀ. ውርደት ለ. ሽልማት ሐ. ክብር መ. ፍርሃት

476.ከሚከተሉት ቃላት አንዱ በቻ መደብ ብዙ ቁጥር ቅርፅ ተቀምጧል።

ሀ. ከፈተ ለ ጀመራችሁ ሐ. በላሁ መ. አደጉ

477. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የድርሰት አካል ያልሆነው የትኛው ነው

ሀ. ተራኪ ለ. መግቢያ ሐ. ሐተታ መ. ማጠቃለያ

478. ከሚከተሉት ውስጥ ግሳዊ ሐረግ የሆነው የቱ ነው

ሀ. አሮጌ ልብስ ለ. ትልቅ ቤት ሐ. ክፉኛ ታመመ መ. ቁልቁለቱን ቶሎ

479. በምክንያትና ውጤት የተያያዘው ዓ.ነገር የቱ ነው ሀ. በጣም ጠገብኩኝ

ለ. ስላጠናሁ ከፍተኛ ውጤት አስመዘገብኩ

ሐ. ሀይለኛ ዝናብ በመዝነቡ ከተማው በጎርፍ ተጥለቀለቀ መ. ለ እና ሐ

480. ሰነፍ ተማሪ ዘወትር ይጨነቃል። የተሰመረበት ቃል ሰዋሰዊ ተግባር ------------------------------ ነው።

ሀ. የስም ገላጭ
ለ. የግስ ገላጭ
ሐ. የቅፅል ገላጭ
መ. ማሰሪያ አንቀፅ

**መመሪያ አርባ አንድ፡- ከጥያቄ ቁጥር 482 -486 የቀረቡትን ጥያቄዎች ከዚህ በታች በቀረበው ግጥም መሰረት መልሱ፡፡**

ቀን ያለፈበት የወደቀ ዕቃ" ጊዜ
ያነሳዋል በጊዜ ሲያበቃ።
ግንበኛ የናቀው ድንጋይ የተጣለ" ውብ ማዕዘን
ይሆናል ከዋለ ካደረ። ጊዜ የጣለውን እንደ እብቅ
አንጉሎ" ጊዜ ያወጣዋል አልማዝ ዕንቁ ብሎ።
በጊዜ የቀረ የለም የታለፈም ባግቦ" በጊዜ ብቅ
ይላል ትዝታን አንግቦ። ጊዜን ሰው አይቀድምም
ጊዜን ሰው አይገታም" ጊዜን
ሰው አይከስም ጊዜን ሰው
አይረታም"
አሻራም የለውም ሲመታም ሲመታም፡፡

**/ከአያልነው ሙላት 'ማን ይሆን የበላ ገጽ 90 የተወሰደ/**

481. ግጥሙ በሳብዕ ቀለም የሚጨርሱ ስንት ስንኞች አሉት
ሀ. አራት ለ. አንድ ሐ. ሁለት መ. አምስት

482. ግጥሙ ያለውን የስንኝና የሀረግ ብዛት በቅደም ተከተል የሚገልፀው የትኛው ነው ሀ. 10 ስንኝና 10 ሐረግ
ሐ. 10 ስንኝና 20 ሐረግ
ለ. 11 ስንኝና 22 ሐረግ
መ. 22 ስንኝና 11 ሐረግ

483. በግጥሙ የመጨረሻ መስመር ሲመታም ሲመታም የሚለው ቃል በሚመለከት ትክክል የሆነው የትኛው ነው
ሀ. አላስፈላጊ የቃላት ድግግሞሽ ነው።
ለ. የግጥሙን ዋነኛ መልዕክት /ጭብጥ/ የያዘ ነው። ሐ. ሁለቱም የሚነበቡት ስልት ተመሳሳይ ነው።
መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

484. እንደ ገጣሚው እምነት የትኛው ትክክል ነው

ሀ. ባለፈ ክረምት ቤት አይሰራም ብሎ ማመን ያስፈልጋል፡፡

ለ. የሰው ልጅ ጊዜን ሊረታውም ባይችልም ሀይሉን ግን ማወቅ አለበት፡፡

ሐ. ጊዜ በሰው ልጅ ሊከሰስም ሊረታም ባይችልም የሰው ሀይል ግን ማወቅ አለበት፡፡ መ. የበደለና የተረሳ ሁሉ ጊዜ ስለሚከሰው ከማዘን መቆጠብ አለበት፡፡

485. የግጥሙ ዋነኛ ትኩረት ምንድን ነው

ሀ. ሰው እን ጊዜ ሀይል የሌለው መሆኑን መግለፅ ለ. ሰው ጊዜን በአግባቡ እንዲጠቀምበት ማሳሰብ ሐ. ለሁሉም ጊዜ እንዳለው መግለፅ

መ. ጊዜ 'በሰው ሲቀድምም" ሊገመትም እንደማይችል መግለፅ

## መመሪያ አርባ ሁለት፡- <u>ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ</u>፡፡

486. ክፍሉ የከብቶች በረት መስሏል፡፡ ይህ ዓ.ነገር የቀረበበት የዘይቤ አይነት____________ ነው፡፡ ሀ. ተለዋዋ ለ. ተምሳሌት ሐ. ተነጻጻሪ መ. አሊጎሪ

487. የኛ ኤሊ ቆሎ ደረስክልኝ፡፡ የሚለው አገላለፅ ከየትኛው ዘይቤ ይመደባል

ሀ. ከምፀት ለ. ከኩሸና ሐ. ከተምሳት መ. ከተነጻጸሪ

488. ልጅቷ ነበር ነች፡፡ ይህ ዓዓነገር የቀረበው በ ________________________ ዘይቤ ነው፡፡

ሀ. ተነጻጻሪ ለ. ተምሳሌት ሐ. አያዎ መ. ተለዋጭ

489. ሰውየው ተራራ አክሏል፡፡ ይህ ዓ.ነገር የቀረበው በየትኛው የዘይቤ አይነት ነው፡፡ ሀ. በተለዋጭ ለ. በግነት ሐ. በተምሳሌት መ. በአያዎ

490. አያቶ አለማየት

የዘመኑ መቅሰፍት በሚለው ግጥም የቀረበው ____________________ ነው፡፡

ሀ. በተለዋጭ ለ. በተነጻጻሪ ሐ. አአያዋ መ. በስመሀዳሪ

491. ከሚከተሉት በተነጻጻሪ ዘይቤ የቀረበው የቱ ነው

ሀ. ልጂቷ ወፍራም ነች

ሐ. ልጂቷ መርዝ ነች

ለ. ልጂቷ አስስት ነች

መ. ልጂቷ ጦጣ ትመስላለች

492. እባክሽ መሬት አንቺ እንኳን፡፡ አድምጭኝ፡፡ ይህ ሀሳብ የቆረጠው ____________ ዘይቤ ነው፡፡ ሀ. በሰውኛ ለ. እንቶኔ ሐ. በተኮሳሌት መ. በንቡር ጠቃሽ

493. የማቱሳላን እድሜ ይስጥሁ፡፡ ይህ ሀሳብ የቀረበው ________________________ ዘይቤ ነው፡፡

ሀ. በሰውኛ ለ. በእንቶኔ ሐ. በተምሳሌት መ. በንቡር ጠቃሽ

494. ለወትሮው ደመና ፊቱ እየጠቆረ

አይኖቹን አሻሽቶ ያነብ ነበር። የሚለው ግጥም የቀረበው______________________ ዘይቤ ነው። ሀ. እንቶኔ　　ለ. ምጸት　　ሐ. ሰውኛ　　መ. ተምሌት

495. ጀንበር ነሽ አበባ ሕይወት ተስፋ ገንቦ፣ ፋሲካ

እንቁጣጣሽ ማሀሌተ ገንቦ።

ሀ. እንቶኔ　　ለ. ምጸት　　ሐ. ሰውኛ　　መ. ተምሳሌት

496. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የተውኔት ሙያዊ ቃል አይደለም

ሀ. ትዕይንት　　ለ. ገቢር　　ሐ. ስንኝ　　መ. ቃለ ተውኔት

497. _______________ የተውኔት ገፀ ባህርያት ማቅረቢያ ዘዴ ነው

ሀ. ጥብጥ　　ለ. ገጸባህሪይ　　ሐ. ቋንቋ　　መ. ጎንታ

498. ዋነኛ ግቡ ሳቅ መጫ የሆነው የተውኔት አይነት የትኛው ነው

ሀ. ቧልተይ　　ለ. ኮሜዲ　　ሐ. ድንቃይ　　መ. ትራጂዲ

499. ዋነኛ ባህርይው ቅይትነት የሆነው የተውኔት አይነት የቱ ነው

ሀ. ድንቃይ　　ለ. ቧልታይ　　ሐ. ኮሜዲ　　መ. ትራጂዲ

500. ገዘገዘ የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉም ሊሆን የሚችለው?

ሀ. ቆረጠ　　ለ. ከረከመ　　ሐ. ፈገፈገ　　መ. ጠረበ